# ሻሎም

አገልግሎቱን፡ የአዲሱ ዓመት ሰብሰባችንን ገና እየጀመርን ነው። ከአዲሱ ዓመት ወዲህ ይህ የመጀመሪያዬ እውነተኛ አገልግሎቴ ነው። ኦህ፡ በቤቴ ጥቂት ምሽቶችን አሳልፌ ነበር፡ ከዚያም ወደዚያ ፎርት ሁዋቹካ ወርጄ ነበር። አሁን እንደዚያ ነው የምትጠሩት? **ሁዋቹካ** በ**ኤች** ፊደል እንዴት እንደሚጻፍ አይገባኝም። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]

2 እናደርገውም፡ እንደ የኋላ-መመልከቻ መስተዋት ዓይነት ነገር አይኖረንም። ወደ ኋላ-የሚያሳይ መስተዋት ወደ ኋላ ብቻ ነው የሚመለከተው የት እንደነበራችሁም ያያል። እኛ ግን የት እየሄድን እንዳለን ለማየት ወደ ፊት እንመለከታለን፡ አያችሁ። ያለፈውን በተመለከተ፡ ጳውሎስ፡ “በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ፡ በክርስቶስ ከፍ ያለውን የመጠራቴን ዋጋ እንዳገኝ ወደፊት እዘረጋለሁ” ብሏል። ማድረግ የምንፈልገውም ይሄንኑ ነው። እንግዲህ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ፊኒክስ ሰመጣ፡ ከአሰራ አምሰት፡ ከአሰራ ሰድሰት ዓመታት በፊት ወዳለው ጊዜ ወደ ኋላ መመልከት እንችላለን፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ብዙ ነገሮች ተከሰተዋል፡ ጥሩም መጥፎም፡ ሁሉም በእግዚአብሔር እጅ፡ ወደ ፍርድ ይገባል። ነገር ግን አሁን ወደ ፊት የምመለከተው በዚህ በሚመጣው ዓመት፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይበልጥ ለማሻሻል ምን አደርጋለሁ፡ ለመንግሥቱ የምችለውን ሁሉ፡ በማድረግ የበለጠ እንዴት እሰራለሁ የሚለውን ነው።

3 አሁን፡ ዛሬ ከሰአት በኋላ ይህንን የአዲሱን ዓመት መልእክት በክርሰቶሰ ላለችው ቤተ ክርሰቲያን መናገር እፈልጋለሁ፡ ከዚያም ነገ ማታ ለታመሙት መጸለይ እንጀምራለን። የጸሎት ካርዶችን እንሰጣቸዋለን... አገልግሎቱ በሰባት፡ ሰባት-ተኩል ላይ የሚጀምር ይመሰለኛል፡ ከቀረው አገልግሎት ጋር ሳትጋጩ፡ የጸሎት ካርዳችሁን ለማግኘት፡ ወደ ሰድሰት ሰዓት፡ ወይም ሰድሰት ሩብ ገደማ እዚህ ብትገኙ የተሻለ ይሆናል።

4 በጉባኤው ፊት፡ ለዚህ ሰብሰባ ይህን ሕንፃ እንድንጠቀም ሰለፈቀዱልን፡ የ—የዚህን የራማዳ አሰተዳደር፡ ማመሰገን እንፈልጋለን። ጌታ ይባርካቸው።

5 አሁንም በቅዱሳት መጻሕፍት ውሰጥ፡ ወደምናነብበት ቦታ መግለጥ ከፈለጋችሁ፡ ከኢሳይያሰ፡ 60ኛው ም—ምዕራፍ፡ 2ኛውን፡ 1ኛውንና 2ኛውን ቁጥር እነባለሁ። መዝሙረ ዳዊት 62፡1-8። በመጀመሪያ፡ መዝሙረ ዳዊት 62፡ 1-8።

> **ነፍሴ ለእግዚአብሔር የምትገዛ አይደለችምን፥ መድኃኒቴ ከእርሱ ዘንድ ናትና።**
>
> **እርሱ አምላኬ መድኃኒቴም ነውና፥ እርሱ መጠጊያዬ ነው፥ እጅግም አልታወክም።**
>
> **እስከ መቼ በሰው ላይ ትቆማላችሁ? እናንተ ሁላችሁ፥ እንዳዘነበለ ግድግዳ፥ እንደ ፈረሰም ቅጥር ትገደላላችሁ።**

**ነገር ግን ክብሬን ይሽሩ ዘንድ፡ መከሩ፥ ሐሰትንም ይወድዳሉ፥ በአፋቸው ይባርካሉ፡ በልባቸውም ይረግማሉ። ሴላህ።**

**ነገር ግን ነፍሴ ሆይ፡ አንቺ ለእግዚአብሔር ተገዢ፥** ተስፋዬ **ከእርሱ ዘንድ ናትና።**

**እርሱ አምላኬ መድኃኒቴም ነውና፣ እርሱ መጠጊያዬ ነው፥ አልታወክም።**

**መድኃኒቴና ክብሬ በእግዚአብሔር ነው፥ የብርታቴም ዓለት፡... መሸሸጊያዬ፡ እግዚአብሔር ነው።**

**የሕዝብ ማኅበር ሁላችሁ፥ በእርሱ ታመኑ፡ ልባችሁንም በፊቱ አፍስሱ፣ እግዚአብሔር ረዳታችን ነው። ሴላህ።**

6 ዳዊት ያንን፡ "ዓለቱ" ብሎ የሚገልጽበት መንገድ ደስ ይለኛል። ካስተዋላችሁ፡ ብዙ ጊዜ፡ "እግዚአብሔር ዓለቴ ነው" ይላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ዓለት ምንን እንደሚያመለክት ታውቃላችሁ? **ዓለት** "መገለጥ" ነው።

7 ጴጥሮስ፡ "አንተ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ" እንዳለው ነው።

8 እርሱም፡ "የዮና ልጅ፡ ስምዖን ሆይ፡ ብፁዕ ነህ። በዚህም ዓለት ላይ፡ በዚህ መገለጥ ላይ... " እግዚአብሔር ገለጠለት። "ሥጋና ደም ይህንን አልገለጠልህም፡ ዳሩ ግን በሰማያት ያለው አባቴ ነው። በዚህም ዓለት ላይ፡ በዚህ መገለጥ ላይ፡ ቤተክርስቲያኔን እሰራለሁ።"

9 ዳዊትም እዚህ ጋር፡ "እግዚአብሔር ዓለቴ፡ መገለጤ ነው" ብሎ ይጮኻል!

10 አሁን በኢሳይያስ 60ኛው ምዕራፍ፡ 1ኛውንና 2ኛውን ቁጥር እንመልከት።

**ብርሃንሽ መጥቶአልና፥ የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና፡ ተነሺ፡ አብሪ።**

**እነሆ፡... ጨለማ ምድርን፡ ድቅድቅ ጨለማም አሕዛብን፡ ይሸፍናል፥ ነገር ግን በአንቺ ላይ እግዚአብሔር** ይወጣል፡ **ክብሩም በአንቺ ላይ ይታያል።**

11 እንጸልይ። ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አሁን በእነዚህ ቃላት ላይ እያሰላሰልን፡ ለክብርህ፡ ይህንን አገልግሎት ልንጀምር ነው። አባት ሆይ፡ ባርከን፡ በኢየሱስ ስም እንጠይቃለንና። አሜን።

12 አሁን፡ የዛሬ ከሰዓት በኋላ ርዕሴ አንድ ቃል ነው፥ **ሻሎም።** በዕብራይስጥ፡ "ሰላም" ማለት ነው። ሰላም፡ ወይም ሰላምታ ነው፡ "ሰላም ለእናንተ ይሁን፡" ወይም፡ "እንኳን ደህና መጣችሁ፡" "እንደምን አደራችሁ" እንደማለት፡ ማንኛውም ዓ—ዓይነት ሰላምታ ነው። ነገር ግን እዚህ በዕብራይስጥ ያገኘሁት ዋናው ቃል፡ ብዙ ትርጉሞች አሉት፡ ዳሩ ግን ሁሉም የሚያመለክተው ያንኑ አንድ ነገር ነው፡ "ሰላም።"

13 ይህንን አዲስ ዓመት ስንቀበል፡ እንዳነበብኩት፡ ጨለማንም ብርሃንንም፡ ሁለቱንም እየተጋፈጥን ነው። አሁን ዳዊት፡ እዚህ ሲናገር፡ "በጌታ ታመኑ።

መታመኛችሁን በእርሱ ላይ አድርጉ፡" እንዳለ እናያለን። ኢሳይያስ፡ "በዚህ ህዝብ ላይ ድቅድቅ ጨለማ ይመጣል፥ ቤተክርስቲያን ግን ተነስታ፡ በብርሃኑ ክብር ታበራለች" ብሏል።

14 ስለዚህ ሌሎች ዓመታትን እንደምንቀበል ሁሉ ይህንንም ዓመት እንቀበላለን፥ ባ—ባለፈው ጊዜ በሰራናቸው ስህተቶች መጸጸት አለ፡ እንዲሁም ወደ ፊት ስለሚመጣው የክርስቶስ ክቡር ብርሃን መጠበቅ አለ። ያለጥርጥር፡ በዚህ ዓመት በሕይወት ከኖርን፡ የሰራናቸውን ብዙ ስህተቶች እናገኛለን፡ ያንንም እንጠብቃለን ምክንያቱም ነገሮች ከጥሩና ከመጥፎ ጎን ስለሚሄዱ ነው። በዚህ ሕይወት ውስጥ ስንኖር የምንገዛበት የነገሮች ተፈጥሯዊ ሂደት ያ ነው። ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ የሚማልድልን መካከለኛ ስላለን፡ እጅግ ደስተኞች ነን። የሰራናቸውን ስህተቶች አምነን ለመቀበል ፈቃደኞች ስንሆን፡ እርሱ ይቅር ይላቸዋል። ለእነዚያ ስህተቶች ይቅር ሊለን፡ በጸጋና በምሕረት የተሞላ ነው።

15 በመጀመሪያ ልናገርበት የምፈልገው፡ ይህ ድቅድቅ ጨለማ፡ ዛሬ በዓለም ውስጥ በብዛት መኖሩንና፡ በማንኛውም ጊዜ እየባሰበትና እየጠቆረ መሄዱን ነው። በመንፈሳዊ አነጋገር፡ በየዓመቱ፡ ዓ—ዓለም ይበልጥ እየጠቆረች መምጣቷን፡ እናያለን፡ ምክንያቱም በጨለማ ውስጥ እየዳበሱ ነውና። ኃጢአት በዝቷል። ያለፍንባቸውን ነገሮች ብቻ ስንመለከት፡ የፕሬዚዳንቱ መገደልና፡ የመሳሰሉትን፡ እንዲሁም እዚሁ አገራችን ውስጥ ሰዎች መገደላቸውን እናያለን። በዘመናዊ ስልጣኔ ጊዜ፡ እንዲህ ያለ ነገር ይፈጠራል ብለን ባናስብም፡ ነገር ግን በእርግጥ ይህ አለን፡ ምክንያቱም በህዝቡ ላይ ድቅድቅ ጨለማ ስለወደቀ ነው። አሁን፡ ወደ ብርሃን ለማይመለሱ ሰዎች፡ ለሚመጣው ዓመት ልናገረው የምችለው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ዓመቱ እየገፋ ሲሄድ ይበልጥ ወደ ጨለማውና ወደ ድቅድቁ እየወረዳችሁ ትሄዳላችሁ።

16 ነገር ግን፡ በዚህ አዲስ ዓመት ወደ ብርሃን፡ ለሚመለሱት፡ ወደምንጠባበቀው ወደዚያ ፍጹም ቀን፡ እርሱ እስኪገለጥ ድረስ፡ ጨለማ ሁሉ ወ—ወደሚወገድበት ጊዜ፡ ይበልጥ እያበራችሁ ትሄዳላችሁ። የዚህም ምክንያት፡ ዛሬ፡ ለሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን፡ "ሻሎም፡" የምልበት ምክንያት፡ እኛ የእርሱ ብርሃኖች ስለሆንን ነው። ኢየሱስ፡ "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" ብሏል።

17 አሁን፡ ነቢዩ፡ "በዚህ ህዝብ ላይ ድቅድቅ ጨለማ፥ በዓለም ህዝብ ላይ፡ ድቅድቅ ጨለማ" ብሏል።

18 በእኔ ዕድሜ አካባቢ ያላችሁ አንዳንዶቻችሁ ወንዶችና ሴቶች፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ፡ በየዓመቱ፡ ያ ጨለማ እንዴት ይበልጥ እየጨመረና እየጨመረ እንደሚመጣ፡ አስተውላችኋል? በቀደም ሰናገር፡ ለባለቤቴ እንዲህ አልኳት፡ "ታውቂያለሽ፡ ዓመታት፡ እያለፉ ሲሄዱ፡ ሰዎች ይበልጥ እየቀረቡት እና እየቀረቡት ሊመጡ ከሚገባቸው እውነተኛው ነገር ይበልጥ እየራቁና እየራቁ የሚሄዱ ይመስላል" አልኳት።

19 በወንዶች መካከል፡ ይህንን አስተውያለሁ። በመንገዶች ላይ ተመልከቱ፡ በአብዛኛው በሴቶች መካከል፡ ፍላጎቶቻቸውንና ምን ማድረግ እንደሚወዱ አስተውሉ፡ አ—አመለካከታቸውን ሁልጊዜ እየቀየሩ ነው። ወንዶች ይበልጥ

እንደ ሴቶች እየሆኑ ነው፡ ሴቶችም ይበልጥ እንደ ወንዶች እየሆኑ ነው፡ ይህንንም ለማስቆም ምንም መንገድ የሌለ ይመስላል። ይህንን ነገር እየተቃወምኩ፡ ሀገሪቱን አቋርጬ አልፋለሁ፡ በሚቀጥለው ዓመትም ስመለስ ከጀመርኩበት ጊዜ ይልቅ የባሰ ሆኖ አገኘዋለሁ። ይኸውላችሁ፡ እነዚያ ሰዎች ትክክለኛውን ነገር ማድረግ ይፈልጋሉ፡ ነገር ግን፡ ትክክል የሆነውን እንዳያደርጉ የሚከለክላቸው፡ የሆነ ነገር አለ። በላያቸው ላይ ይጫናቸዋል፡ ያስገድዳቸዋል። በ—በመላው ምድር ላይ እንዳለ ከባድ፡ ጨለማ ጉም ነው። በፊኒክስ ብቻ ሳይሆን፡ ነገር ግን በዓለም ሁሉ ላይ፡ እውነተኛውን ወንድነትንና እውነተኛውን ሴትነትን በማፈን፡ ሁልጊዜ፡ ይበልጥ እየወፈረና እየወፈረ የሚሰበሰብ፡ የጨለማ ስብሰብ፡ ያለ ይመስላል። እየተናገርኩ ያለሁት በተፈጥሮአዊው መንገድ ነው።

20 እንግዲህ፡ እነርሱ፡ ያም ነገር… ይበልጥ ወደ አብያተ ክርስቲያናት እየገባ ያለ ይመስላል። ከዚያም ተነስታችሁ ይህንን በሚጻረር መልኩ የሆነ ነገር ስትናገሩ፡ ይህን በማድረጋችሁ ይኮንኗችኋል። አያችሁ፡ ሲ—ሲመጣ ልታዩት ትችላላችሁ፡ ከ—ከዚያም ስትቃወሙት፡ የሆነ ሰው በተሳሳተ መንገድ ይረዳዋል። አንዳንዴ ሴቶች በተሳሳተ መንገድ ይረዱታል፡ ወንዶች በተሳሳተ መንገድ ይረዱታል፡ የተሳሳተ አመለካከትም ይይዛሉ።

21 ወንዶች አንዳንዴ፡ ጥሩ ወንዶች፡ አባል በሆኑበት በሃይማኖታዊ ተዋረድ ውስጥ ያላቸውን ስፍራ ለማስጠበቅ እንዲህ ካሉ ነገሮች ጋር መላመድ ይኖርባቸዋል፡ ምክንያቱም፡ ያንን ካላደረጉ፡ ይወገዳሉ፡ ከዚያም የ—የራሳቸውን መንገድ ይከተላሉ። ከአንድ ህዝብ ዘንድ አንዴ ከተወገዱ በኋላ፡ ከዚያም ወደ ሌላ መግባት ከባድ ይሆናል፡ ምክንያቱም ከዚህኛው ሌላ ቡድን ጋር አብራችሁ እንደነበራችሁ አንዴ ካወቁ፡ ያኔ፡ "**እዚህ** ምን ተፈጥሮ ነው" ይላሉ? ስለዚህ በእምነታችሁ ጸንታችሁ መቆም፡ ወይም በራሳችሁ መንገድ መሄድ፡ ወይም ደግሞ እምነታችሁን መካድ ይኖርባችኋል። ስለዚህ ይህ በህዝቡ ላይ በጣም ከባድ ያደርገዋል።

22 አሁን ጊዜው፡ ልክ እውነተኛ ወንድ መሆን እንዳለበት አይነት፡ እውነተኛ አቋም ማየት የማትችሉበት ይመስላል። እ… ከመንፈሳዊው፡ ወደ ተፈጥሯዊው፡ መለስ ብለን ስንወስደው እንኳ፡ እ… ወንዶች ቬልቬት ሮዝ ጫማዎችንና፡ የመሳሰሉትን ነገሮች ሁሉ ሲለብሱ ሳይ፡ ይበልጥ እንደ ሴቶች የሆኑ ይመስለኛል። ሴቶችም ሲጋራዎችን ሲያጨሱ፡ አሁን ሲጋራ ይዘው፡ ዝም ብለው… ጸጉራቸውንም እንደ ወንድ ይቆርጣሉ፥ ያ ውብ—የሴትነትና፡ የእመቤትነት ጸጋ፡ የጠፋ ይመስላል። እውነተኛው ወንድነትም እንዲሁ ጠፍቷል፥ የሚያስበው ነገር ሁሉ በሌላኛው ገጽታ፡ ክፉ ነገር ብቻ ይመስላል።

23 ልክ በመጀመሪያው እንደነበረው ይመስለኛል፡ "በሰው ልብ ውስጥ ያለው አሳብ ሁሉ ዘወትር ክፉ ይሆናል።" ፕ—ፕሮግራሞቻችን፡ ቴሌቪዥንና—ራዲዮ፡ ያልታረሙ ናቸው። ሰዎች የሚፈልጉትን ማንኛውንም ነገር፡ ማለት ይቻላል፡ ሊናገሩ ይችላሉ፡ በመጠጥ ቤት ውስጥ እንኳ መባል የሌለበትን፡ የ—የማይባለውን፡ የማይገባውን ቆሻሻ፡ ጸያፍ ቀልዶችን ለምሉና ሊሳደቡ ይችላሉ። ነገር ግን በቴሌቪዥንና በራዲዮ ላይ ሊናገሩት ይችላሉ፡ በቀጥታም ወደ ሰዎች ቤቶች ይልኩታል። ያ ድቅድቅ ጨለማ ነገሩን ሁሉ የሸፈነው ይመስላል። ዓለም ሁሉ የተበከለች ትመስላለች።

24 አሁን፡ ለዓመታት፡ የእግዚአብሔርን ቃል፡ ደረጃ ለመጠበቅ ሰሞክር ነበር። በዚህ በሚመጣው ዓመት በሕይወቴ ውስጥ አድርጌው ከማውቀው በላይ ያንን ደረጃ ለመያዝ ይበልጥ ቆርጫለሁ፡ እያችሁ፡ ከቃል ጋር በትክክል ለመቆም። አሁን፡ ይህን የማደርገው ብልጥ ለመምሰል ነው ብሎ የሚያስብ ማንም ሰው ቢኖር፡ እንደዚያ ከሆነ፡ ወንድሜ፡ እህቴ፡ በእርግጥ ተሳስታችኋል ብዬ እሰባለሁ። ይህን የማደርገው ግዴታ ስላለብኝ ነው። እኔ፡ ከዚያ ቃል ጋር ለመቆየት ግዴታ አለብኝ። የሚናገረውን ማንኛውንም ነገር፡ ምንም የግል ትርጓሜ ሳልሰጠው፡ በቃ በዚያው መንገድ እናገረዋለሁ። አሁን ሊተረጉሙትና ትንሽ ለየት ያለ እንዲመስል ሊያደርጉት የሚችሉ አንዳንዶች ሊኖሩ ይችላሉ፡ ነገር ግን እኔ ያንን ማድረግ አልችልም። የማውቀው ብቸኛው ቋንቋ እዚህ ላይ የተጻፈው ብቻ ነው፡ ልክ እዚህ ባለበት መንገድ።

25 አሁን፡ ጥቂት፡ አሁን፡ ሦስት ዓመት ገደማ ይሆነዋል፡ ይህም፡ በቤቴ፡ በቤቴ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡ መንፈስ ቅዱስ ተናገረኝ፡ “ወደ ቱክሰን ሂድ፡ የሚጠብቅህ ነገር አለ፡” አለኝ። በዚህ መድረክ ላይ ቆሜ ለሁላችሁም እንዲህ አልኳችሁ፡ “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ አንድ ነገር ሊከሰት ተቃርቧል” አልኳቸው። ያንን የሚያውቁ ምናልባትም በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እዚህ ተቀምጠዋል። ያየሁትን ብቻ ነው የነገርኳችሁ። መልእክቱ በቴፕ ተቀርጿል፡ **ሰንት ሰዓት ነው፡ ጌታዬ?** ልክ እ—እንደ ፒራሚድ፡ የመላእክት ሰብሰብ፡ ከቱክሰን በስተሰሜን በኩል ሲወርድ አየሁ፥ **በዚህ** በኩል ወደ ላይ፡ ከቱክሰን በስተሰሜን በኩል ነበር። እነርሱም የሆነ ነገር ተናገሩኝ፡ ምን እንደሆነም አላወቅሁም ነበር። አንድ ቀን እዚያ... አሁን እዚህ አብረውኝ የተቀመጡ፡ ያ ነገር ሲከሰት፡ እዚያ አብረውኝ የነበሩ፡ ሁለት ሰዎች አሉ።

26 በሰማይ ላይ ያለውን ምስሉን አነሱት። በ—በመጽሔትም ላይ ወጥቷል። ኮፒው ያለኝ መሰሎኝ ነበር። አለኝ። ይሄውና። እዚህ **በላይፍ** መጽሔት ላይ፡ በዚህ ቅጂ ላይ ታዩታላችሁ፡ ልክ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሆን በተናገረው መንገድ ነው።

27 እነዚያም ሰባት መላእክት ልክ እኔ እዚህ ቆሜ እንደምታዩኝ በተፈጥሮአዊ ሁኔታ በዚያ ቆመው ነበር፡ ወደ ቤቴም እንድመለስ ነገሩኝ፡ ይህም፡ በዘመናት መካከል የነበሩት ተሐድሶ አድራጊዎች ሊያገኙዋቸው ያልቻሉት ሚስጥሮች፡ ሰባቱ ማኅተሞች የያዙዋቸው፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ሚስጥሮች፡ እንደሚገለጡ ነገሩኝ። እነዚያን **ሰባት ማኅተሞች** ወስዶ እንዲመለከታቸውና፡ በእነርሱ ላይ ስህተት እንዲያገኝ፡ ማንኛውንም ሰው እሞግታለሁ። እያችሁ? እያችሁ? ምክንያቱም በእግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነት የተሰጠ ነውና።

28 ከዚያ በፊት፡ ስለ **ሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት** ሰብኬ ነበር፡ ከዚያም ተበርናክል ውስጥ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ሰያቸው ነበር።

29 ትምህርቴ እቋም፡ እዚህ ውጭ ትምህርትን አልሰብክም፡ ከታላላቅ የወንጌል መሠረታዊ ጉዳዮች በስተቀር ምንም አልሰበኩም፥ ምክንያቱም ከእኔ ጋር ሊቃረኑ ከሚችሉ፡ ወንድሞች ጋር ስለሆንኩ፡ ያንን እዚህ በሰዎች ፊት አልሰጥም። እንደምናምነው ባሉት፡ በእውነተኛዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ መሰረታዊ ትምህርቶች ላይ ብቻ ለመቆየት እሞክራለሁ። ነገር ግን፡ ተበርናክል

ውስጥ፡ በቴፕ ይቀዱታል። ከፈለጋችሁት፡ ልታገኙት ትችላላችሁ። ፓስተራችሁ እንድትወስዱት ካልፈለገ፡ አትውሰዱት። እያንዳችሁ፡ ያ የእናንተ ውሳኔ ነው።

30 ነገር ግን በዚያ ውስጥ፡ ስለ **ሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት** ስሰብክ፡ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ማረጋገጫ ለማግኘት፥ እንዴት ጨለማ ወደ ቤተክርስቲያን እንደገባ፡ ኒቂያ፥ እንዲሁም የቤተክርስቲያኒቱ መላእክትን፡ መልእክተኞቹን በሰዕል ሳወጣቸው ነበር። ልክ መሆን ነበረበት፡ ምክንያቱም፡ በእሁድ ጠዋት፡ በአስራ አንድ ሰዓት ላይ የመጨረሻውን የቤተክርስቲያን ዘመን ስዬ ልክ እንደጨረስኩ፡ ያ ታላቅ ብርሃን፡ እዚህ እንደተቀመጡት ሰዎች ያህል በሚሆኑ ሰዎች ፊት፡ ወደ ሕንፃው ወረደ፥ ወርዶም በእነዚያ ሁሉ ሰዎች ፊት፡ በግድግዳው ጎን ላይ እራሱን እያብለጨለጨ፡ እነዚያን የቤተክርስቲያን ዘመናት ልክ እዚያ በሳልኳቸው መንገድ ሳላቸው። አሁን፡ ያንን የሚያረጋግጡ በመቶዎችና በመቶዎች የሚቆጠሩ ምስክሮች በዚያ አሉ። ብቻ...

31 መልካም፡ አሁን፡ እግዚአብሔር ነገሮችን በምድር ላይ ከማሳየቱ በፊት ሁልጊዜ በሰማይ ላይ እንደሚያሳይ እንገነዘባለን። ልክ ጠቢባን ኮከቡን እንደተከተሉና፡ ወዘተ ነው። በመጀመሪያ፡ ሰማያዊ ምልክት ይከሰታል፡ ከዚያም ምድራዊው ያንን ሰማያዊ ምልክት ያጸናዋል። እግዚአብሔር፡ በምልክቶች ይሰራል፡ በምልክቶችና በድንቆች ይሰራል። እነርሱም በሁሉም ቦታ የሚያምኑትን ይከተላሉ። አይሁዶች የእግዚአብሔር ምርጦች ስለነበሩ፡ ሁልጊዜ ምልክትን ይፈልጉ ነበር፡ ምልክትንም ይጠብቁ ነበር። “ምልክቱን አሳዩን፡ ከዚያም እናምናለን።” እና፡ ከዚያም፡ ሰብአ ሰገል፡ ስለ ክርስቶስ ልደት ያላቸውን፡ ታሪክ ይዘው እነዚያ የጥበብ ሰዎች ሲመጡ፡ ልክ በአዲሱ ዓመት ነበር።

32 አሁን ጨረቃ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ቤተክርስቲያንን እንደምትወክል እናውቃለን። ፀሐይ በሌለችበት ጊዜ፡ በምድር ላይ ብርሃንን ታሳያለች። ራእይ፡ 12ኛው ምዕራፍ፡ ይህንን፡ “ጨረቃ ከእግሮቿ በታች፡ ፀሐይም በራሷ ላይ ያላት ሴት” በማለት በሚገባ ያብራራል። ፀሐይ በሌለችበት ጊዜ፡ ፀሐይ ወደ ሌላኛው ወገን ስትሄድ፡ ጨረቃ የፀሐይን ብርሃን ወደ ምድር እንዴት እንደምታንጸባርቅ ጭምር ያሳያል። የእግዚአብሔር ልጅ በሌለበት ጊዜ፡ ቤተክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስን ለዓለም ልታንጸባርቅ ይገባታል። ሁላችንም ያንን እናምናለን። ብዙ ነገሮች የተለዩ እንደነበሩት ሁሉ፡ ይህ እንግዳ ነገር ነው።

33 ነገር ግን በ1933፡ ጳጳሱ፡ ከሰፍራው ስለመንቀሳቀሱ፡ ወይም፡ ማለትም፡ ከሮም ስለመውጣቱ፡ እንዲሁም ወ—ወደ ቅዱሳን ሰፍራዎች ጉብኝት ስለማድረጉ እዚህ ሰናገር ነበር። ወደዚህም ይመጣል። ስለዚህም የተፈጠረው እንግዳ የሆነ ነገር፡ ይህ ነው፡ እርሱ ሮምን ለቆ ከመውጣቱ ከጥቂት ምሽቶች በፊት፡ በታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ ጨረቃ ወርዳ ሙሉ ግርዶሽ ውስጥ ገባች። በቃ፡ ምን ነበር? የልጁን የሚያንጸባርቅ ብርሃን መጋረድ ነው። በዚህ ውስጥ፡ ለኦርቶዶክስ ፓትርያርክ ተናገረ፥ ሁሉም ተስማምተዋል፥ “ጳጳሱ ይህንን የሚያደርገው ለኅብረት ነው፡ ለጥሩ የጎረቤት ኅብረት።” ይህም፡ ለተፈጥሯዊ ጆሮ፡ ሊሆን ከሚችለው እጅግ ድንቅ ነገር ሆኖ ይሰማል። ሆኖም ለመንፈሳዊ ጆሮ፡ ጨለማ ነው። ታዲያ እኛ አብያተ ክርስቲያናት፡ እኛ ፕሬስባይቴሪያን፡ ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ እንዲሁም ጴንጤቆስጤዎች፡ መጽሐፍ ቅዱሳችን የተለየ ትምህርት እንደሚያስተምረን እያወቅን፡ ወደ እንደዚህ ዓይነት

ውጥንቅጥ ውስጥ እንዴት ልንገባ እንችላለን! በመንፈስ-የተሞላ ሰው፡ በዚያ ተቀምጦ እንዲህ ብሎ መናገሩ ለእኔ አስገራሚ ነገር ነው፡ "በእንደዚህ ዓይነት ስፍራ በመገኘቴ መንፈሳዊነት ተሰምቶኛል።" ይህ ለእኔ፡ እጅግ ዘግናኝ ነው።

34 አሁን፡ እዚህ ፊኒክስ ውስጥ እንዳገኛችሁት እገምታለሁ። ማንኛውም ሰው... እነዚያን የቤተክርስቲያን ዘመናት ስዕሎች ስስል እዚህ ውስጥ ያያችሁ ስንቶቻችሁ ናችሁ? እጆቻችሁን አንሱ። ሰገምት... በቀደም ማታ፡ ጌታ በሰማያት ላይ እንዴት እንደሳላቸው አይታችኋል? ልክ እዚያ ተበርናክል ውስጥ በተሳለበት መንገድ ነበር። ከሶስት ዓመታት በፊት፡ በተብርናክል ውስጥ መንፈስ ቅዱስ፡ በመንፈስ አነሳሽነት፡ በሰጠበት መንገድ በትክክልና ፍጹም በሆነ ሁኔታ፡ እዚያ በሰማያት ላይ ተከሰተ። "በሁለት ወይም በሶስት ምስክሮች አፍ፡ ቃል ሁሉ ይጸናል።" በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ በመንፈስ አነሳሽነት ተንቀሳቀሰ፥ በመድረኩም ላይ ሳልኳቸው። ከዚያም እርሱ እራሱ ወረደና ማረጋገጫውን ሰጠ፡ ልክ ጨረቃና ብርሃኑ እየጠፉ፡ እየጠፉ ሲሄዱ፡ እንዲሁም ይህ የሎዶቅያ ዘመን ዳግም ወደ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ሲገባ አሳየ። ቤተክርስቲያናት ሁሉ በቤተክርስቲያናት ፌዴሬሽን ጥምረት ውስጥ፡ አንድ ላይ በሚሆኑበት ልክ በዚያው ጊዜ፡ እዚህም ወርዶ በጨረቃ ላይ ያጸናዋል።

35 ኢሳይያስ፡ "በምድር ላይ፡ በዚህ ህዝብ ላይ ድቅድቅ ጨለማ ሆኗል" ማለቱ፡ ምንም አያስገርምም።

36 ድርጅትን መቃወም ተቀባይነት እንደሌለው አውቃለሁ፡ ነገር ግን ያ የአውሬው ምልክት ነው። እኛን በቀጥታ ወደዚያ እየወሰደን ያለው ነገር እርሱ ነው። ለአውሬው ምስል እያደረገ ነው። ያንን የምናገረው ተናድጄ አይደለም። ወንድሞች ሆይ፡ ያንን የምናገረው እውነት ስለሆነ ነው። ፊኒክስ የምትነሳበት ቀን ይመጣል፡ ምናልባትም እኔ አልፌ እሄድ ይሆናል፡ ነገር ግን ያ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** እንደነበረ ታውቃላችሁ። እውነት ነው። ታላቁ መንፈስ ቅዱስም እነዚያን መልእክቶች እንዴት እንዳጸናና ነገሮችን እንዴት አስቀድሞ እንደተናገረ፡ አንድም ጊዜ እንኳን ሳይወድቅ! ታዲያ ለምን በጨለማ ውስጥ እንዳብሳለን? ጊዜው ከማለፉ በፊት ሰዎች ለምን አይነቁም? ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ ምልክቱን ወስዳችሁ ስትጨርሱ፡ ጊዜው ያረፍዳል፡ ከዚያም ምንም... ከዚያ በኋላ ልታደርጉት የምትችሉት ሌላ ምንም ነገር የለም፡ በዚያ መዋቅር ውስጥ ትያዛላችሁ፡ በዚያ መዋቅርም ትታተማላችሁ።

37 ለምን ወደ ክርስቶስ አትመጡም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ብርሃን፡ ነፃ ሊያወጣችሁና በተራራ ላይ እንደተቀመጠች መብራት ሊያደርጋችሁ በሚችለው፡ በትንሳኤው ኃይል አትሞሉም? ምንም ያህል ቢጨልምም ችግር የለውም። እንዲህም ትላላችሁ፡ "እንግዲህ፡ ለምን እናደርገዋለን? የተቀሩት... " አዳምጡኝ፡ አሁን በጣም በጨለመበት ጊዜ፡ ሊያበራ የሚገባበት ጊዜ ነው። ብርሃን ይበልጥ የሚያበራው፡ በጨለማ ውስጥ ሲሆን ነው። ሁልጊዜ ጨለማ በሆነበት ስፍራ ብርሃን እንዲበራ ማድረግ አለብን።

38 ነቢዩ፡ "በዚህ ህዝብ ላይ ድቅድቅ ጨለማ ይሆናል" ማለቱ፡ በእርግጥም እውነት ነው።

39 አሁን ጨረቃ ብርሃኗን እንድታንጸባርቅ ያደረጋት ምን እንደሆነ ደርሰንበታል። እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ በጥቁር ሰሌዳ ላይ አሳየ፥

ቀጥሎ፥ በራሱ ህልውና፥ ከዚያም በሰማያት ላይ ምልክቱን አሳየ። ከዚያም ጳጳሱ ከሮም ወጥቶ፡ ወደ ፍልስጤም ሄደ፥ ይህም፡ በተራው ሰው ዕይታ፡ ሰዎች እየጮኹ በግንባራቸው ተደፉ፡ ሰውዬውንም እመለኩ። ከእንደዚህ ዓይነት ጋር ከሚተባበር አገልጋይ ይልቅ በእርሱ ላይ ምንም የተለየ ተቃውሞ የለኝም። ሁሉም ያው አንድ ዓይነት መንፈስ ነው።

40 ያ ድቅድቅ ጨለማ በህዝቡ ላይ ያረፈ ይመስላል ይህም ሊያሰቡት የሚገባው ሊያደርጉ የሚገባው ብቸኛው ነገር ወደ ቤተክርስቲያን መሄድና በጣም ጥሩ ሰው መሆን፡ ሰማችሁን በመዝገብ ላይ ማሰፈር፡ እንዲሁም አንዲት ሚሰጢራዊ ነገር ላይ ያደርጋል ይላሉ፡ “ሰትሞቱ እግዚአብሔር ቁልፉን ከፍቶ፡ በውስጣችሁ ያለውን ያንን መንፈስ፡ ወደ ራሱ ይቀይረዋል።” ተሳስታችኋል። ሰትሞቱ፡ በእናንተ ላይ ያለው ያ መንፈስ፡ ለዘላለም የምትሆኑት እንደዚያው ነው። እስታውሱም፡ ፈሪሳውያን፡ ሰዱቃውያንና፡ የመሳሰሉት፡ እጅግ ሃይማኖተኛ ሰዎች ነበሩ።

41 እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነው፡ እርሱ ቀናተኛ ነው፡ ሚስቱም ንጽህት እንድትሆን ይፈልጋል፡ ድንግል፡ ንጽህት፡ ከዓለም የሆነ ምንም ነገር በውስጧ የሌለባት፡ ሙሉ በሙሉ ቃሉ፡ የእርሱ አካል እንድትሆን ይፈልጋል፡ የቃሉ አካል መሆን አለብን። የሐይማኖት መግለጫ አካል ሳይሆን፡ የቃሉ አካል፥ የቤተክርስቲያን አካል ሳይሆን፡ የሙሽራይቱ አካል። ቤተክርስቲያን ተኮንናለች፡ ወደ ውጭው ጨለማ እንደምትሄድ እናውቃለን፡ ነገር ግን ሙሽራይቱ ወደ ላይ ትወጣለች።

42 አሁን ሰዎች ለጥቂት ጊዜያት ነቅተው ያ ታላቁ ነገር ምን እንደሆነ ቢገነዘቡ ኖሮ። ያንን የሚያደርገው ትዕቢት ነው። እንደቀረው ዓለም መሄድ የ—የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው። ያንን ማድረግ አይገባም። ከዓለም አይደላችሁም። በሬሳ ሳጥን ውስጥ የተኛች ሴት ፀጉሯን ዋተር-ዶድ መሰራት ያምራታልን ወይም ምን ነበር የምትሉት፡ ብቻ ምንም ይሁን ትፈልጋለችን? በሬሳ ሳጥን ውስጥ ገብታ ስለ አለባበሷ ታስባለች ብላችሁ ታስባላችሁን፡ ወይም ሌላ ወንድ ያሰባልን? አያደርጉትም።

43 ዛሬም፡ ከጎረቤቶቻችን፡ ወይም ከአንዳንድ የሆሊውድ ኮከቦች፡ ወይም ከአንዳንድ ፋሽኖች፡ ወይም ከመሳሰሉት ነገሮች፡ ልንኮርጃቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች ያሉበት ምክንያት ይኸው ነው፡ ምክንያቱም ለክርሰቶስና ለቃሉ ገና አልሞትንም። የቤተክርስቲያናት ችግር ምንድነው? በጨለማ ውስጥ ነን፡ በጨለማ ውስጥ እየዳበሰን ነው። “በህዝቡ ላይ ድቅድቅ ጨለማ ይሆናል፡” ብሏል። አሁን በህዝቡ ላይ ድቅድቅ ጨለማ ሆኗል!

44 ይህ ሁሉ ምን ማለት ነው? ይህ ማለት ይህ ነው፡ ዓለም ሲ... ጨረቃ እንድትጠፋ ያደረጋት፡ ምክንያቱም የ—የፀሐይ... ምድር እራሷን በምድር ላይ ከምታንጸባርቀው፡ ከፀሐይ ጥላ ውስጥ ሰለገባች ነው። ዓለም በጥላው ውስጥ ገብታለች። የቤተክርስቲያኒቱም ችግር ያ ነው። የፕሬስባይቴሪያን፡ የሜቶዲስት፡ የጴንጤቆስጤዎች ችግር ያ ነው። የሁላችንም ችግር ያ ነው። ዓለም እኛ ልናንጸባርቅ የሚገባንን ብርሃን ትዘጋለች፡ ዙሪያዋን ትሽከረከርና በውስጡ ትገባለች፡ እናም፡ እርስ በእርሳቸውም ሲተላለፉ፡ በላዩ ላይ ጨለማን ትጥላለች።

45 ዓለምም በ—በየሐይማኖት ተቋም ሰም፡ በእንዳንድ የሐይማኖት መግለጫ ሰም፡ ወደ ቤተክርሰቲያን ገብታለች፡ “እኛ ሃይማኖተኞች ነን **ይሄ** ሁሉ **ይሄ** ሁሉ” ትላለች፡ ዳሩ ግን ለዚህ ዘመን የተተነበየውን ቃሉን የሚያጸናውን የክርሰቶሰን የትንሳኤ ኃይል ትክዳለች። ብርሃን ሊኖር የሚችለው በእግዚአብሔር ቃል በኩል ብቻ ነው። ያንን እናውቃለን። እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ “ብርሃን ይሁን፡” አለ፡ ብርሃንም ሆነ፡ ይህም የተናገረውን ቃሉን ማጽናት ነበር።

46 ጥቁረት፡ ተጋረደ! ዓለም ከፀሐይ ወደ ጨረቃ ከሚያንጸባርቀው ብርሃን ጋር ተሰለፈች፡ እጨለመችውም። በተፈጥሯዊው፡ ወይም በመንፈሳዊው የሆነው በትክክል ያ ነው። በተፈጥሯዊው እንደሆነው፡ አሰቀድሞ እንዳሳየንና እንደነገረን፡ በትክክል የሆነው ያ ነው።

47 አሁን፡ በመጨረሻ ያ እንዴት እንደሚሆን አያችሁ። ብዙዎቻችሁ ወጣቶች፡ ለማንኛውም፡ ሌላ ሶሰት ወይም አራት ዓመታት በሕይወት ከኖራችሁ፡ ያንን ለማየት ብዙ ማርጀት አያሰፈልጋችሁም።

48 አሁን ጨረቃ፡ እኛ በሎዶቅያ የቤተክርሰቲያን ዘመን ውሰጥ ነን። ከሌሎች ቤተክርሰቲያናት ሁሉ፡ በሎዶቅያ የቤተክርሰቲያን ዘመን፡ በዚያች የሎዶቅያ፡ በመጨረሻዋ፡ ለብ ባለችው የቤተክርሰቲያን ዘመን፡ ክርሰቶሰ ከቤተክርሰቲያን ውጭ ነበር። ማንኛውም መጽሐፍ ቅዱሰ አንባቢ ያንን ያውቃል። ራእይ 3፡ ከቤተክርሰቲያን ውጭ ሆኖ፡ ዳግም ወደ ውሰጥ ለመግባት መንገድ እየፈለገ ነበር፡ እንደገባም ከቶ አልተናገረም። “ዳሩ ግን የሚወዳቸውን ሁሉ፡ ይገሰጻል ይቀጣልም።” መልእክቱ እርሱ የሚወዳቸውን ይገሥጻል እንዲሁም ይቀጣል። አሁን፡ እያንኳኳ፡ ለመግባት እየሞከረ ነበር፥ ጨለማው ዘጋው፡ በትክክል የተከናወነው ያ ነው። ሲያበራ የነበረው ብርሃን፡ በቅርቡ በፍጹም ሙሉ በሙሉ ይዘጋል። ለአውሬው ምሰል ለመፍጠር ሁሉም ወደዚያ ውሰጥ ይገባል። ይህ ምን ማለት እንደሆነ እናውቃለን፡ ይህ የመጨረሻው ዘመን ነው።

49 እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ ብርሃንን ከጨለማ ለየ፡ አሁንም እግዚአብሔር እያደረገ ያለው ያንኑ ነው። እግዚአብሔር ብርሃንን ከጨለማ ይለያል። “በመጀመሪያ፡” እንዲህ አለ፡ “ብርሃን ይሁን” አለ። አሁን፡ አሰታውሱ፡ ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ ምንም ብርሃን ሊኖር አይችልም። ውጭ ያለችው ያቺው ፀሐይ እራሷ፡ የተገለጠች የእግዚአብሔር ቃል ናት። በምድር ላይ ድቅድቅ ጨለማ ነበረ፡ በምድር ላይ ጉምና ጭጋግ ነበረ፡ እግዚአብሔርም፡ “ብርሃን ይሁን” አለ። አሁን ብርሃን ባይመጣ ኖሮሰ? ታዲያ መናገሩ ምንም ጥቅም አይኖረውም ነበር። ነገር ግን “ብርሃን ይሁን፡” ባለ ጊዜ፡ ብርሃንም ወደ መኖር ሲመጣ፡ ቃሉ ትክክል መሆኑን አረጋገጠ። ዛሬ የምንኖርበት ብርሃን ያ ነው።

50 ዛሬም፡ በቤተክርሰቲያን ውሰጥ ሊኖረን የሚችለው ብቸኛው ብርሃን፡ እግዚአብሔር ብርሃኑን ለዚህ ትውልድ ያረጋገጠው ብርሃን ነው።

51 እያንዳንዱ ትውልድ የተወሰነ ድርሻ ተመድቦለት፡ በዘመናቸውም ብዙ ነገር ሆኗል። ሁላችንም ያንን እናውቃለን። ነቢያት ወደ ሁኔታው ይመጣሉ። ለእነርሱ፡ የጌታ ቃል ወደ እነርሱ መጣ፡ ተረዱትም። በብሉይ ኪዳን፡ **ባለ ራእይ** ማለት፡ “ቃሉ የተገለጠለት ሰው፡” ማለት ነው። ያንንም እንዴት

ያውቁታል፡ ምክንያቱም እርሱ የሚመጡትን ነገሮች አስቀድሞ ያውቃል። ከዚያም በእያንዳንዱ ዘመን የጌታ ቃል ወደ እነርሱ መጣ።

52 ኢየሱስ፡ ስለ ዮሐንስ ሲናገር፡ “እርሱ ለጥቂት ጊዜ፡ የሚያበራና የሚያንጸባርቅ ብርሃን ነበረ” አለ። ለምን? ኢሳይያስ፡ እርሱ ከመወለዱ ከሰባት መቶ አስራ ሁለት ዓመታት በፊት፡ “በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ አለ፡” ብሏል። ሚልክያስ፡ 3ኛው ምዕራፍ ላይ፡ “እነሆ፡ መንገዴን በፊቴ እንዲያዘጋጅ፡ መልእክተኛዬን እልካለሁ፡” ብሏም። አያችሁ፡ እርሱ ያ የጸና ቃል ነበረ። ለዚያ ዘመን የተሰፋ ቃል የተሰጠው ቃል፡ እርሱ ብርሃን ነበረ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለ እርሱ የተናገረውን ያንኑ ቃል ወደ ፍጻሜ እያመጣው ነበረና።

53 ኢየሱስም በመጣ ጊዜ፡ ዮሐንስ፡ “አሁን እኔ ልደበዝዝ ይገባኛል፥ እርሱ ሊታይ ይገባዋል” አለ። እርሱም ብርሃን ነበረ። በዘመናት ሁሉ፡ እግዚአብሔር ያ ዘመን ስለመምጣቱ ብዙ ጊዜ ተናግሮ ነበር!

54 እነዚያ የሐይማኖት አባቶች ያንን እንዴት ሊያዩት አልቻሉም? እንዴት ተሳናቸው? እነዚያ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ማየት እንዴት ተሳናቸው? እርሱም፡ “በእነርሱ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታስባላችሁና፡ ቅዱሳን መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ፡ እነርሱም ስለ እኔ ይመሰክራሉ” አለ። ወንድሞች ሆይ፡ ያንን ማየት እንዴት ተሳናቸው? ምክንያቱም እንደሚያደርጉ ትንቢት ተነግሮ ነበርና።

55 ዛሬም እንዲሁ ነው፡ ያ ድቅድቅ ጨለማ በህዝቡ ላይ እየመጣ ነው፡ እኛም ይሄው እዚህ ነን! እግዚአብሔር ቃሉ በዚህ ዘመን እንዲገለጥ ወስኗል፡ ያለንም ብቸኛ ብርሃን እርሱ ነው፡ እግዚአብሔርም አንድ ሰው ያንን ቃል እንዲገልጥ ያደርጋል። አንድ ሰው ያንን ያደርገዋል። ተሰፋ ሰጥቷል፡ ሁልጊዜም በእርሱ በኩል ያደርግ እንደነበረው በትክክል ይሰራል።

56 እርሱ የአሠራር ሰልቱን ፈጽሞ አልለወጠም። ምን እንደሚሆን ይተነብያል፡ ከዚያም አንድን ሰው ይልክና ያንን ያረጋግጣል። ያ በሚሊዮኖች ጭንቅላት ላይ ያልፋል፡ ምክንያቱም፡ በዚያን ጊዜ ጨለማ ምድርን ይሸፍናልና። ሰዎች ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ይወዳሉ፡ ምክንያቱም ጨለማ ብዙ ደስታ አለውና።

57 በቅርቡ፡ የሆሊውድ ተውኔት አይቼ ነበር፡ “ሕይወት የሚጀምረው ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ ነው፡” ይላል። ያኔ ነው ሞት የሚጀምረው፥ እነዚህ የምሽት ክለቦች ሁሉ፡ እየኖሩ ያሉ በሚመስላቸው ሰፍራዎች ሁሉ። እየሞቱ ነው።

58 እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ ብርሃንን ከጨለማ ለየ። እርሱ ሁልጊዜ ያንን አድርጓል። ምን ያደርጋል? ያንን ይገፋዋል፡ በሚመጣው ብርሃን አማካኝነት፡ ጨለማውን ወደ ሌላኛው የምድር ክፍል ይገፋዋል።

59 አሁን ሊፈጸም ያለው ያው ነው። ልክ ቀኑ ከመውጣቱ በፊት ነው። የንጋት ኮከብ የቀኑን መምጣት ለማብሰር ወጥቷል። መንፈስ ቅዱስም ብርሃኑን እያሳየ ነው። ብርሃንና ጨለማ፡ አንዱ ከሌላው የሚለዩበት ጊዜ እየመጣ ነው። ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ የዘመኑን ሥርዓት ይከተላሉ፥ ክርስቶስና የብርሃን-ቃሉ ተሰፋ ግን በንጥቀት ውስጥ ያልፋሉ። ለእነርሱ የቀራቸው ብቸኛ ነገር ያ ነው። ዛሬ፡ ዘመኑ፡ እርሱ መምጣቱን ለሚጠባበቁ ብዙዎች፡ የአዲስ ቀን ንጋት ነው።

60 ዛሬ በጣም ብዙ፡ ቅን የሆኑ ሰዎች አሉ፡ ልባቸውን የሚያቃጥለውም ይኸው ነው፡ ልክ እንደ ማርያምና ዮሴፍ ያሉ በጣም ብዙ፡ ቅን ሰዎች አሉ። ከበዓሉ እየተመለሱ ነበር፡ ኢየሱስንም አጡት። ዛሬም ብዙ ሰዎች ከእነርሱ ጋር ያለ እየመሰላቸው፡ ያንኑ ያደርጋሉ። አሁን፡ የእግዚአብሔር ቃል ምን ያህል የማይሳሳት እንደሆነ ላሳያችሁ፡ ይህችን ትንሽ ብርሃን ላበራላችሁ እወዳለሁ።

61 ዛሬ ከሰዓት በኋላ፡ እዚህ ያለን ሁላችንም፡ ክርስቲያኖች የሆንን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠው፡ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ እናምናለን። ከድንግል እንደተወለደም እናምናለን። እርሱ ሁሉን ቻይ አምላክ እዚህ ምድር ላይ ያደረበት፡ ማደሪያው ነበር። ነቢይ ብቻ አልነበረም፡ ተራ ሰውም ብቻ አልነበረም፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ራሱ በሰው አምሳል የተገለጠበት እንጂ። እርሱ **አማኑኤል፡** "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" ነበር። ያንንም፡ በሙሉ ልባችን እናምናለን። አሁንም አስታውሱ ማርታ ማ…

62 ማለትም፡ ማርያምና፡ ዮሴፍ፡ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር የነበረ ስለመሰላቸው፡ ከእነርሱ ጋር መሆኑን ገምተው፡ "ምንም ችግር ሊኖር አይችልም። እርሱ ከእኛ ጋር መሆኑ አይቀርም፡" ብለው አስበው ነበር። ነገር ግን በሚያሳዝን ሁኔታ ተሳስተው ነበር። አልነበረም።

63 ዛሬም በጣም ብዙ፡ ጥሩ ሰዎች ልክ እንደዚሁ ናቸው። ያስባሉ፡ ሰዓቱ እየቀረበ መሆኑን ያያሉ፡ የሆነ ነገር ሊሆን እንደሆነ ያውቃሉ፡ ታዲያ ምን ያደርጋሉ? እርሱ ከእነርሱ ጋር ያለ እየመሰላቸው፡ ሄደው ቤተክርስቲያንን ይቀላቀላሉ። ማድረግ ያለባቸው ያ ብቻ እንደሆነ አስበው፡ "እርሱ ከእነርሱ ጋር ነው" በማለት፡ ከሰባኪው ጋር ይጨባበጣሉ። በተወሰነ መንገድ ተረጋግጠው ወይም ተጠምቀው፡ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ነው በማለት፡ ማድረግ ያለባቸው ያ ብቻ እንደሆነ ያስባሉ። ወንድሜ፡ እህቴ፡ ልክ እንደ የቀድሞዎቹ፡ ማርያምና፡ ዮሴፍ፡ በእውነት ቅን ሰዎች ሆነው ሳሉ፡ ነገር ግን ተሳስተው ነበር።

64 ኢየሱስ ከእናንተ ጋር መሆን አለመሆኑን ህይወታችሁ ያረጋግጣል። ህይወታችሁ እርሱ **እዚህ** በውስጣችሁ ማደሩን፡ ወይም አሁንም በሰማያት መሆን አለመሆኑን፡ ማንም ብትሆኑ ያሳያል። "የማደርገውን ስራ እናንተም ታደርጋላችሁ።" እንዴት ክርስቶስ በውስጣችሁ ኖሮ፡ በውስጣችሁ ያለው ያ መንፈስ የእርሱን ቃል ክዶ፡ በምትኩ የሐይማኖት መግለጫ ሊቀበል ይችላል? ሊያደርገው አይችልም። የገዛ ቃሉን በመካድ ራሱን ያሸንፋል።

65 አንድ ሰው የተሳሳተ ትርጉም ስለሰጠው ብቻ? መጽሐፍ ቅዱስ አላችሁ፡ እንደማንኛውም ሰው ማንበብ ትችላላችሁ። ቅን ሁኑ።

66 ዳዊት፡ "እርሱን ሁልጊዜ በፊታችሁ አድርጉት" ብሏል። ይህንን አዲስ ዓመት ስንገናኝ፡ የምንገናኘው በክርስቶስ የትንሳኤ ኃይል መሆኑን እወቁ። "እርሱ ሁልጊዜ በፊቴ ነውና። አልታወክም።"

67 የቃሉ አለመውደቅ ምን ያህል እንደሆነ አስተውሉ። ማርያምና ዮሴፍ… አሁን ለእናንተ፡ ውድ የካቶሊክ ወዳጆቼ፡ ማርያም የእግዚአብሔር እናት ነበረች የምትሉ አዳምጡኝ። ማርያም የእግዚአብሔር እናት መሆኗ ቀርቶ፡ የኢየሱስ እናት እንኳን አልነበረችም። እንዴት ልትሆን ትችላለች? ትክክል ነው። አንድ ጊዜ እንኳን እናቴ ብሎ አልጠራትም፥ በጭራሽ።

68 አንድ ጊዜ ወደ እርሱ መጥተው፡ “እናትህና ወንድሞችህ በውጭ ቆመዋል፡” አሉት።

69 እርሱም በጉባኤው ላይ ተመለከተና፡ “እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው፡” አለ? ደቀ መዛሙርቱን ተመለከተና፡ እንዲህ አለ፡ “የአባቴን ፈቃድ የሚያደርጉ፡ እነርሱ እንደ እናቴና፡ እንደ... ”

70 በመስቀል ላይ፡ እየሞተ በነበረበት ጊዜም፡ ያንኑ ነገር ተናገረ። ዮሐንስን እንዲህ አለው፡ “ዮሐንስ ሆይ፡ **እነሆ**፡ ልጅሽ፡ እነሆ እናትህ!” “እናቴ ሆይ፡ እነሆ ልጅሽ፡” አላለም። “አንቺ ሴት፡ እነሆ ልጅሽ” አለ! አልነበረችም፡ አያችሁ፡ የእግዚአብሔር እናት አልነበረችም።

71 እግዚአብሔር የተጠቀመበት የተውሶ ማህፀን ብቻ ነበረች፥ እግዚአብሔር ሊጠቀምባት ካሰባት ሌላ ሴት በምንም አትበልጥም። እርሱ ልጁን ለመግለጥ፡ ብ—ብቻ እንዲያደርገው ከፈቀዳችሁለት፡ (የእናንተን) የልባችሁን ማህፀን ሊጠቀም ይችላል። አያችሁ? የአምላክ እናት አትባልም። የማርያም ዘር ለመሆን እንኳ፡ የሆነ ስሜት መኖር ነበረበት። እርሱ ከማርያም የተገኘ ዘር እንኳ አልነበረም።

72 ሙሉ ነገሩ፡ ፈጣሪ፡ እግዚአብሔር፡ ነበር። የመጀመሪያው አዳም ያለ አባትና እናት ከተፈጠረ፡ ሁለተኛው አዳምም እንደዚያው ነበር። ከዚያ የሚያንስ ማንኛውም ነገር ከእርሱ ጋር እኩል አያደርገውም። በትክክል። ያው እግዚአብሔር፡ እርሱ ራሱ የሚያድርበትን ስጋ ፈጠረ።

73 አሁን፡ እዚህ ጋር ያለውን፡ ተመልከቱ፡ ማርያም የእግዚአብሔር እናት ከነበረች፡ እዚያ ጋር፡ እንዴት እንደተሳሳተች ተመልከቱ። “እኔና አባትህ እያለቀስን ስንፈልግህ ነበርን፡” አለች። ከድንግል መወለዱን በመካድ፡ “እኔና፡ አባትህ፡ ዮሴፍ፡ ስንፈልግህ ነበርን” አለች።

74 ያን የአስራ-ሁለት-ዓመት ልጅ፡ የአስራ-ሁለት-ዓመት ህፃን፡ “እዚያ ላይ ካሉት የሐይማኖት ተቋማት ጋር እየተከራከርኩ፡ በአባቴ ጉዳይ ልሆን እንደሚገባኝ አታውቁምን፡” ሲል ተመልከቱ? አሁን፡ በዮሴፍ ጉዳይ ላይ፡ ቢሆን ኖሮ፡ እዚያ ታች በአናጢው ቤት ይሆን ነበር። ዮሴፍ አባቱ አልነበረም። እግዚአብሔር አባቱ ነበር። “በአባቴ ጉዳይ ልሆን እንደሚገባኝ አታውቁምን? ” እዚያ ላይ፡ በአስራ ሁለት ዓመቱ፡ ከተማሩት ካህናት ጋር ነበር። አንድም ቀን እንኳ ትምህርት ቤት አልገባም፡ ነገር ግን በጥበቡ ተገርመው ነበር። ተመልከቱ...

75 እርሱ ቃል ነበር። ሲወለድ፡ ቃል ነበር። አሁንም ቃል ነው። አስተውሉ፡ ቃሉ ሀሰተኛን ነገር አይቀበልም። እርሷም፡ “እኔና አባትህ እያለቀስን ስንፈልግህ ነበርን” አለች።

76 “የግድ በአባቴ ጉዳይ ላይ መሆን እንዳለብኝ አታውቁምን፡” አለ?

77 ለምንድን ነው እናቱን እንኳ የገሰጻት? ለምን? እርሱ ቃል ነበር። በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡ ምክንያቱም ማርያም፡ በአንድ ወቅት “መንፈስ ቅዱስ” ጋረደኝና ልጅ ወለድሁ ብላ የነበረች ስትሆን፡ አሁን ደግሞ አባትህ ዮሴፍ ብላ ትጠራዋለች። ቃሉ ግን አይሳሳትም። ሊወድቅ አይችልም።

78 “በአባቴ ስራ ላይ መሆን እንዳለብኝ አታውቁምን? ” እርሱም በአባቱ ጉዳይ ላይ ነበር፥ በ—በዮሴፍ ጉዳይ ላይ አይደለም፡ በ—በሮችና አናጢነትን በመስራት ላይ አልነበረም። በአባቱ ጉዳይ ላይ ነበር፡ በዚያ ዘመን የነበረውን የሐይማኖት ፖለቲካ በማቃናት ላይ ነበር። “በአባቴ ስራ ላይ መሆን እንደሚገባኝ አታውቁምን? ” አዎን፡ ወዳጄ።

79 ዛሬ ብዙ ሰዎች፡ ከእነዚህ ጥሩ ከሚባሉ ቤተክርስቲያናት ብዙዎቹ፡ ወደዚያ የቤተክርስቲያን ምክር ቤት እየገቡ ነው፥ “እየገቡ” አይደለም፡ እዚያ ደርሰዋል። ማድረግ ያለባቸው ነገር በትክክል ያ እንደሆነ እያሰቡ ነው፡ “ወዳጃዊ ነው፡ ጥሩ ነው፡ ሁላችንም በአንድ ላይ ለምን አንሆንም? ” ለምን፡ ሁሉንም፡ ለዓመታት፡ ሁሉንም ሜቶዲስቶች ባፕቲስት፡ ሁሉንም ባፕቲስቶች ፕሬስባይቴሪያን፡ ለማድረግ ሲሞክሩ ቆይተዋል፥ ጴንጤቆስጤዎችም ሁሉንም ጴንጤቆስጤ ለማድረግ ሞክረዋል። ያንን ማድረግ አትችሉም፡ ነገር ግን ምክር ቤት ለእናንተ መልሱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያደርጉት የሚናገረው፡ መልሱ ያ ነው፡ ያደረጉትም በትክክል ያንኑ ነው። ወዳጃዊ ቤተክርስቲያናት፡ አዎን፡ ወዳጄ፡ አንድ ላይ መሰብሰብ ነው፡ “ጥሩ ነው፡ ኅብረት እናድርግ!”

80 መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ “ሁለት ሰዎች ካልተስማሙ በቀር እንዴት አብረው ይጓዛሉ? ”

81 ከእነርሱ አንዳንዶቹ ከድንግል መወለዱን ይክዳሉ። ሰማንያ በመቶ የሚሆኑት የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያናት ከድንግል መወለዱን ይክዳሉ። የመንፈስ ቅዱስንም ጥምቀት ይክዳሉ። የመምጣቱን ምልክቶች፡ የትንሳኤውን ኃይል ይክዳሉ። እርሱ ትናንት፡ ዛሬም፡ እስከ ዘላለምም ያው መሆኑን ይክዳሉ። እግዚአብሔር በአንድ ወቅት አንዲት ሴት የቃሉን አንድ ትንሽ ክፍል በመጠራጠሯ ምክንያት ይህን ሁሉ ምስቅልቅል ወደ ዓለም አምጥቶ ሳለ፡ እናንተ እንዴት መካድ ትችላላችሁ? ሰይጣን ከአንድ ነገር በስተቀር፡ ሁሉንም እውነት ነግሯት ነበር፡ ነገር ግን ያ ሁሉንም ችግር ያመጣው ያ አንዱ ነገር ነበር። አሁን፡ ይህ የምታዩት የልብ ስብራትና ሀዘን ሁሉ የመጣው፡ አንዲትን ትንሽ ክፍል በመጠራጠር ምክንያት ከሆነ፡ አንድ ትንሽ የጥርጥር ክፍል ወደ መንግስቱ የሚያስገባን ይመስላችኋልን?

82 ኢየሱስ ንጽህት ለሆነች ድንግል፡ እድፈት ለሌለባት፡ በመንፈስ ቅዱስ ለተሞላች፡ የዓለም ሳትሆን፡ የእግዚአብሔር ኃይል ለሆነች ድንግል የሚመጣበት ምክንያት ይኸው ነው። ኦህ፡ ወደዚህ ቡድን መግባት የሚቻል መሆኑን ማወቅ እንዴት ድንቅ ነው! እንዴት ነው የምታደርጉት? ድርጅትን በመቀላቀል ፈጽሞ አታደርጉትም። ይህን የምታደርጉት በመንፈስ ቅዱስ ስትጠመቁ፡ ወደ ሚስጥራዊው የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ውስጥ ስትገቡ፡ ከእርሱ ጋር በትንሳኤ ስትነሱ፡ ከሞትና ከኃጢአት ነፃ ስትወጡ ነው። ብቸኛው መንገድ ያ ነው።

83 ጨለማ! ታላላቅ የሐይማኖት ተቋማት፡ ትልልቅ ሰዎች በአንድነት ተሰብስበው ስለ እርሱ የራሳቸውን ሀሳብ ያስቀምጣሉ፡ ያም በመጀመሪያው እንደነበረው ዓይነት ውዥንብር ውስጥ መልሶ ይከታችኋል። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ምንም ተስፋ የለም፥ ዝም ብላችሁ ጠፍታችኋል። ሁሉም ስለ እነዚህ መልካም ቤተክርስቲያኖች በጣም የተነሳሱ ይመስላሉ፡ እግዚአብሔር ከእነርሱ

ጋር የሚሆን ይመስላቸዋል። “ደህና፡ ካውንስሉ እዚያ ላይ በአንድነት ሲሰበሰብ፡ ኤኩሜኒካላዊ እንቅስቃሴዎችና የመሳሰሉት ሁሉ ሲኖሩ፡ የሺህ ዓመቱ ግዛት ይጀምራል፡” እያሉ ይቀላቀላሉ። ምን እያደረጉ ነው? ለአውሬው ምስል እያደረጉ ነው፡ አብረዋቸው የማይቀላቀሉት የሐይማኖት ተቋም አባል ያልሆኑትንና፡ የመሳሰሉትን ሁሉ፡ ወደ ውጭ የሚጣሉበትን፡ ኃይል እየሰሩ ነው። ያ የሚሆን መሆኑን ዝም ብላችሁ ተመልከቱ።

84 ያንኑ ዕለት፡ ጽፌው ነበር… ጌታ በ1933 ያንን እንዳየው አድርጎኛል። ጳጳሱ ሮምን እንዴት ለቅቆ እንደሚወጣ ልክ እርሱ… ቃሉ እንዳለው፡ ልክ በተመሳሳይ መንገድ፡ እየመጣ ያለው፡ እዚህ ላይ ነው።

85 አሁን፡ ሁለቱም ጥሩ ሰዎች ናቸው፡ ነገር ግን ተሳስተዋል። ዮሴፍና ማርያም መልካም ሰዎች ነበሩ፡ ነገር ግን በእጅጉ ተሳስተው ነበር። ሆኖም ይህ ምን ነበር? እግዚአብሔር የአስራ-ሁለት-ዓመት ልጅን የተጠቀመው ያ ቃል ንጹህ ሆኖ መቆየት እንዳለበት ለማሳየት ነው፡ ልክ እንደነበረው፡ ከመጀመሪያውም እንደተናገረው፡ “ከድንግል የተወለደ ነው፡” እንደዛውም ነበር።

86 ቤተክርስቲያናትንና፡ የመሳሰሉትን ሲቀላቀሉ እርሱ ከእነርሱ ጋር የነበረ መስሏቸው ነበር፡ ዳሩ ግን አልነበረም። አሁን፡ ነገር ግን ለተመረጡት… አሁን፡ ያ ጨለማ ነው፡ እኔም በእርሱ ላይ ለሌላ አንድ ሰዓት መቆየት እችላለሁ።

87 ነገር ግን ለተመረጣችሁ፡ ክቡራንና ለተጠራችሁ፡ የእግዚአብሔር ቅዱሳን፡ በዚህ በሚመጣው አዲስ ዓመት፡ እንዲህ እላችኋለሁ፥ ሻሎም፡ የእግዚአብሔር ሰላም!

88 ዘመኑ አሁን ነው! ዓለም ከመፈጠሯ በፊት በነበሩት ዘመናት ወደኋላ ሄጄ፡ ወደ ታችም አይቼ ሁሉን ነገር ብመለከት፡ አብም እንዲህ ቢለኝ፡ “በየትኛው ዘመን መኖር ትፈልጋለህ? ” ብሎ ቢጠይቀኝ፡ አሁኑኑ እል ነበር! ዘመኑ አሁን ነው! ይህ ቤተክርስቲያን ከገባችባቸው ሁሉ ታላቅ ዘመን አንዱ ነው፡ ሙሽራው ከመምጣቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ያለው ዘመን ነው። ኑህ፡ እውነተኛዋ የህያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን፡ የወንገሉ ብርሃን በመካከላቸው ጸድቆ ሳለ በእሳት የተያያዘች፡ የምትነድ ልትሆን ይገባታል። “ተነሺና አብሪ፡ ብርሃንሽ መጥቷልና፡” የዚህ ዘመን ብርሃን። ኢሳይያስ የዘመኑ ብርሃን ነበር። ኖኅ የዘመኑ ብርሃን ነበር። ለምን? ቃሉ ተገልጦለት ነበር። ወንጌልም፡ የዚህ ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት፡ የዘመኑ ብርሃን ነው። እየኖርንበት ያለው ዘመን እንዴት ያለ የክብር ዘመን ነው!

89 አሁን፡ “እንደምን አደራችሁ” ማለት **ሰላም** ማለት ነው። ጨለማ እየተሰበሰበ ነው። ለምንድነው የሚሰበሰበው? ብርሃንን ለማሳየት ነው። ኢሳይያስ 60:1፣ “ተነሺ አብሪ፡ ብርሃንሽ መጥቷልና” ብሏል። “ሻሎም” ማለት የቻልኩት ለዚህ ነው፡ ብርሃኑ ወደ እናንተ መጥቷል፡ የእግዚአብሔር ሰላም ለተመረጠችው ሴት፡ ለተመረጠችው እመቤት ይሁን፥ እግዚአብሔር፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት ለጠራቸውና፡ ለዚያ ላዘጋጃቸው ነው።

90 የተቀሩት ፈጽሞ አያዩትም። ስለእርሱም ምንም አያውቁም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚያ ይላልና። ኢየሱስም እንዲህ አለ፡ “አብ አስቀድሞ ካልሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም፥ አብ የሰጠኝም ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።” ያ…

91 ይሁዳ በዚያ ሆኖ፡ ብርሃኑ **እዚህ** ላይ እየበራ ነበር፡ በልቡ ውስጥ ግን የጨለማ ዘር ነበር። የመጨረሻው የውሳኔ ሰዓት ሲመጣ፡ ጨለማው ታየ።

92 **እዚህ** ፊት ለፊት፡ ሙሉ በሙሉ የጠቆረች፡ አንዲት ትንሽ፡ አሮጊት ሴት ነበረች፥ ነገር ግን **እዚህ** ታች አስቀድሞ የተወሰነ ዘር ነበረ። ብርሃኑም ሲመጣ፡ ጨለማውን በታተነው፡ እርሱም ታየ። "መሲሕ እንደሚመጣ እናውቃለን፡ ሲመጣም፡ እነዚህን ነገሮች ያሳየናል፡" አለች።

ኢየሱስም፡ "እኔ እርሱ ነኝ" አላት።

93 ዳሩ ግን ይሁዳ ተጠራጠረው፡ ቢሆንም በብርሃኑ ውስጥ እየተመላለሰ ያለ ይመስል ነበር። አያችሁ፡ **እዚህ** ላይ ያለው ብርሃን ምንም አይደለም፥ ዋናው ነገር **እዚህ** ታች ያለው ብርሃን ነው። **እዚህ** ላይ ያለው ብርሃን ይራመዳል ህብረት ያደርጋል፡ ሌሎች ነገሮችንም ሁሉ ያደርጋል፥ ነገር ግን እውነተኛው የእግዚአብሔር ኃይል ሲገባ፡ **ወደዚህ** የሞተ ዘር ሊመለስ አይችልም፡ በየሐይማኖት ተቋሙ ውስጥ ተንፀባርቆ ያልፋል።

94 ዳሩ ግን **እዚህ** ታች ሲሆን፡ እውነተኛ፡ አስቀድሞ የተወሰነ ዘር፡ ያ ብርሃን እዚህ ታች ሲወርድ፡ ጨለማውን ሁሉ ከእናንተ አርቆ ያሳያል፡ ከክርስቶስም ጋር ህብረት ውስጥ ያስገባችኋል። ዓለም ሳይፈጠር በፊት ህይወትን የሰጣችሁ እርሱ ነበር፡ አለበለዚያ እግዚአብሔር ያለውን ነገር፡ ፈጽሞ አታዩትም ነበር።

95 አሁን፡ ለተወሰናችሁ ዘር፡ ሻሎም! አሜን። አሁን ወደ መጨረሻው ስለቀረብን፡ የእግዚአብሔር ሰላም በእናንተ ላይ ይረፍ። አሁን ወደ መጨረሻው በጣም ቀርበናል። ለተወሰነ ጊዜ፡ ስለዚያ ቡድን እንነጋገራለን። ሻሎም!

96 የእግዚአብሔር ብርሃን መጥቷል። የዚህን ዘመን የእግዚአብሔርን የተሰፋ ቃል መገለጫዎች ማየት እንድትችሉ፡ የብርሃን፡ ቃል፡ እንደገና ተረጋግጧል። "መጻሕፍትን መርምሩ፡ በእነርሱ የዘላለም ህይወት ያላችሁ ይመስላችኋልና።" እነርሱ ስለምንኖርበት ዘመን ይመሰክራሉ። የዘመኑ ብርሃን ምንድነው? መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ዘመን ተሰፋ የሰጠው ምንድነው? የምን ዘመን እንደሆነ ተመልከቱ!

97 ኢየሱስ ዮሐንስን ሰላላመኑት ቢገስጻቸው ምንም አያስደንቅም። ነቢዩ እንደሚመጣ ተናግሮ ስለነበር፡ እርሱ ብርሃን ነበር። የተገለጠውም ብርሃን፡ እርሱ እዚያው ነበር። አላዩትም ነበር። ሊረዱትም አልቻሉም፥ መሲሕ መስሏቸው ነበር፡ **እነርሱ** ሌላም ነገር መስሏቸው ነበር፡ **ይህ** ደግሞ ሌላ ነው። ማየት ተስኗቸው ነበር።

ኢየሱስ ቀጠለ። ሁለት ብርሃኖች በአንድ ጊዜ ሊያበሩ አይችሉም።

98 የቤተክርስቲያን ብርሃንና የእግዚአብሔር ብርሃን በአንድ ጊዜ ሊያበሩ አይችሉም። የቤተክርስቲያንን ብርሃን የሚያጠፋው የእግዚአብሔር ብርሃን መሆን አለበት። ዛሬም እየሆነ ያለው ያው ነው። እግዚአብሔር ቤተክርስቲያናዊነትን እኛ እየኖርንበት ካለው የዚህ ዘመን የተሰፋ ቃል ከሆነው የእርሱ ብርሃን እየለየው ነው። ወዳጄ፡ እውነቱ ይህ ነው። ያንን ማመን አትፈልጉ ይሆናል፡ ነገር ግን እውነት መሆን አለመሆኑን ዝም ብላችሁ ጠብቁና እዩ። አትጠብቁ፡ ለመግባት ዕድሉ እያለ አሁንውኑ ብትገቡ ይሻላችኋል።

99 ቃሉ ሲጸና ብርሃን ነው። ቃሉ፡ ለዘመኑ ተሰፋ የተሰጠው ቃል፡ እስከሚጸና ድረስ፡ ብርሃን አይደለም። ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር፡ “ብርሃን ይሁን” ቢልና፡ ፀሐይ ወደ መኖር ባትመጣ፡ የብርሃን ምልክት የለም። ነገር ግን እግዚአብሔር ግን፡ “ብርሃን ይሁን” ሲል፡ ብርሃን ሆነ። እግዚአብሔር መሲሕን ተሰፋ ሲሰጥ፡ መሲሕ መጣ፡ ከዚያም ቃሉ ተፈጸመ የዘመኑም ብርሃን እርሱ ነበር። ኖኅን ተሰፋ ሲሰጥ፡ ሌሎችንም ተሰፋ ሲሰጥና፡ ወደታች ሲቀጥል፡ እነርሱ የዘመኑ ብርሃን ነበሩ።

100 ዛሬም የዘመኑ ብርሃን አለ፡ ያም በትንሳኤው ኃይል ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡ ለዚህ ዘመን ተሰፋ የተሰጠው የእርሱ ቃል ነው። “እኔ የማደርገውን ስራ፡ እናንተም ታደርጋላችሁ፥ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፡ ከዚህ የሚበልጥ ታደርጋላችሁ።” ከእርሱ ይልቅ የሚበልጥ ስራ፡ የሚበልጡ ነገሮች? ታምኑታላችሁን? እኔ አምነዋለሁ። ትሁት ይመስላል። በሰዎች ጭንቅላት አልፏቸው የሚሄድ ይመስላል። እዚህ ምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ተመልከቱ፡ “የሚበልጡ” ስራዎችን እንዴት ልታደርጉ ትችላላችሁ? ያንን ብዙ ጊዜ፡ “ብዙ፡” ብዬ ተርጉሜዋለሁ፡ ነገር ግን ያው ነው። በዮሐንስ 14፥12 ላይ፡ “የሚበልጥ” አለ፡ “ከዚህ የሚበልጥ ስራ ትሰራላችሁ” አለው።

101 አስተውላችኋል? ውሃን ወደ ወይን ጠጅ ሊለውጥ ሲሄድ፡ በመጀመሪያ፡ ውሃን ወሰደ፥ አስቀድሞ የተፈጠረን ነገር ወሰዶ፡ ወደ ወይን ጠጅ ለወጠው። አምስት ሺህ ሰዎችን ሲመግብ፡ በአንድ ወቅት በውሃ ውስጥ ይዋኝ የነበረውን ዓሣ ወሰዶ፡ ቆርሶ፡ ሰጠ፡ ፍጥረትንም አበዛ። በአንድ ወቅት ስንዴ የነበረውን፡ ተጋግሮ ዳቦ የሆነውን ዳቦ ወሰዶ፡ ቆርሶ ሰጠ... ለህዝቡ ሰጠ፡ እርሱም ተመልሶ መጣ። ፍጥረትን አበዛ!

102 በመጨረሻዎቹ ቀናት ግን፡ ምንም የፍጥረት ምልክት በሌለበት፡ እንዴትም፡ በመናገር ይፈጥረዋል፡ በመጀመሪያ የነበረው ያው አምላክ መሆኑንም ያሳያል። እግዚአብሔር ስለሆነ፡ ሽኮኮዎችን መፍጠር ይችላል፡ የፈለገውን ሁሉ መፍጠር ይችላል። “እኔ ወደ አባቴ እሄዳለሁና፡ ከዚህ የሚበልጥ ታደርጋላችሁ።” ቃሉ የማይሳሳት ነው፡ ሊገለጥና ሊፈጸምም ይገባዋል። “ከዚህ የሚበልጥ ታደርጋላችሁ፡” በማብዛት ሳይሆን፡ ነገር ግን ወደ ፍጥረት መናገር ነው።

103 ተሰፋ ሲሰጥ ቃሉን ተመልከቱት። ታዲያ፡ የት ነው፡ የት ነው ያለነው? እየኖርን ያለነው በየትኛው ዘመን ነው? ዘመኑስ ምንድነው? እንደሁሉም ዘመናት፡ የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ ነው። **ሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት** የሚለውን መልዕክት ሰምታችኋል። ወጥተው የነበሩት እያንዳንዳቸው አውሬዎችና፡ የተከተሏቸው አውሬዎች እንዴት እንደነበሩ በትክክል ተመልከቱ። ልክ ቃሉ እንዳለው ልክ መሆን በነበረበት መንገድ፡ በተሐድሶ አራማጆች ዘመንና፡ በየዘመኑ ሁሉ፡ በትክክል መምታቱን ተመልከቱ። ዛሬም መንፈስ ቅዱስ ልክ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለው በትክክል ይገለጣል።

104 በሰማያትና በምድር ያሉትን ጥላዎችና፡ ነገሮችን ሁሉ፡ ምክር ቤቶችንና እየተዘጋጁ ያሉትን ነገሮች እናያለን።

105 በዚያ ሁሉ መካከል፡ ለዚህ ዘመን የተሰጠው የተሰፋ ቃል፡ የከበረው የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል፡ ራሱን ሲገልጥ፡ እናያለን። የምንኖረው በሚያስደንቅ

ዘመን ውስጥ ነው። የዚህን ዘመን ቃል ለመስማት፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት ለተመረጣችሁና፡ በልባችሁ ውስጥ ቃል ላላችሁ ሁሉ ሻሎም። ለእናንየ ላልሆናችሁ ግን፡ ከፊታችሁ ያለው ዘመን መጥፎ ነው። ከሆናችሁ ደግሞ፡ ከፊታችሁ ታላቅ ዓለም አለ፡ ወይም ታላቅ ዘመን፡ ታላቅ ዓመት፡ አዲስ ዓመት እየመጣ ነው።

106 አዲስ ገጽ ለመግለጥ አይደለም፥ ብዙ ሰዎች በአዲስ ዓመት አዲስ ገጽ ለመግለጥ ይሞክራሉ፡ በሚቀጥለው ቀን ደግሞ መልሰው ወደኋላ ይገልጡታል።

107 በቀደም በጠዋት እያነበብኩት እንደነበረው ትንሽ ታሪክ ነው። አንዲት ሴት በማለዳ ተነስቶ ወጥቶ የጠዋቱን ጋዜጣ አምጥቶ እያነበበ ወደ ነበረው ባለቤቷ፡ ጮክ ብላ ተጣራች፡ እርሱም የጠዋት ጋዜጣ እያነበበ ነበር። እንዲህ አለ... እርሷም፡ “በዜናው ውስጥ አዲስ ነገር አለ” አለች?

እርሱም፡ “የለም፡ ያው ነው፡ የተለዩት ሰዎቹ ብቻ ናቸው” አላት።

108 ዛሬም ያለው ሁኔታ እንደዚሁ ነው፡ ያው ነው። አዲስ ድርጅት ይከፈታል፡ ያው አሮጌው ትምህርት ነው፥ ዝም ብለው ያሻሹታል፡ አንድ ሰው የተወሰነውን ክፍል **በዚህ** ወይም **በዚያ** መንገድ እንዲሄድ ያደርገዋል።

109 ይህ አዲስ ዘመን ነው። ሃሌሉያ! ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ተነስተን፡ የምናበራበት ዘመን ነው። ድቅድቅ ጨለማ በምድር ላይ አርፏል፥ ለእኛ አዲስ ቀን ሊሆንልን ይገባል፡ አዎን፡ እርግጥ ነው፡ እርሱ በሚያደርገው መንገድ ብቻ ማድረግ አለብን። ዳሩ ግን ወደ ቃሉ ተመልሳችሁ ለዚህ ዘመን የተሰጠውን የተሰፋ ቃል ተመልከቱ፡ ያኔ በብርሃን ዘመን ውስጥ እየኖራችሁ መሆን አለመሆናችሁን ታውቃላችሁ። ካለንዳር መቀየር ጊዜውን አይቀይረውም፥ ካለንዳር ብቻ ነው የሚቀይረው።

110 አሁን በደምብ አዳምጡ። ዳዊት እንዳደረገው አድርጉ፡ የወደፊት ጊዜያችሁን በእጁ ላይ ጣሉት። “እንዴት? ምን ማድረግ እንዳለብኝ እንዴት አውቃለሁ፡ ወንድም ብራንሐም? ” የወደፊት ጊዜያችሁን በእጁ ላይ ጣሉት። ምንም ቢመጣ ወይም ቢሄድ፥ በእርሱ ታመኑ። እርሱ ቃል ነው፡ ይህንን አሁን እወቁ። ዳዊት፡ “ጊዜው በእጄ ነው። ሁልጊዜ በእርሱ ታመኑ። ዘወትር በእርሱ ታመኑ” አለ። የወደፊቱን ማን እንደያዘ፡ ዳዊት ያውቅ ነበር፡ ይህንን ሊናገር የቻለውም ለዚህ ነው። የወደፊቱን የያዘው አንድ ብቻ ነው፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ፡ እርሱ የ—የወደፊቱን ይዟል፡ እናንተንም እንዲይዛችሁ ፍቀዱለት። መልካም።

111 አንዳንድ ሰዎች፡ “ነገር ግን፡ ወንድም ብራንሐም፡ ሞክሬያለሁ ደግሜ ሞክሬያለሁ” ይላሉ።

112 ነገር ግን ቆይ ልንገራችሁ። ትዕግስት ሀይል ነው። ትዕግስት የመንፈስ ቅዱስ ሀይል ነው። “እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ።”

113 እናንተም፡ “እንዴት ከዚህ በላይ ልጠብቅ እችላለሁ” ትላላችሁ? ዝም ብላችሁ ጠብቁ። ለመቆም የምትችሉትን ሁሉ ካደረጋችሁ በኋላ፡ ከዚያ ቁሙ፡ እያችሁ፡ ዝም ብላችሁ ቁሙ። “እንዴት ላደርገው እችላለሁ? ” ቁሙ! እውነት

ነው ብሏል፡ እውነትም ነው። ይሆናል ብሏል። “እንዴት? ” አላውቅም፥ ነገር ግን ይሆናል። ተናግሯል። ተሰፋ ሰጥቷል። ተሰፋ ከሰጠ፡ ይሆናል ማለት ነው። ያ ነው በቃ። ሊባክን አይችልም።

114 ስለዚህ አሁን ይህንን አስታውሱ፡ እግዚአብሔር ስለሚመጣው አዳኝ የሰጠውን ተሰፋ ለመፈጸም በሺዎች የሚቆጠሩ ዓመታት ወሰዶበታል። ያንን ተሰፋ ለመፈጸም፡ እግዚአብሔር አራት ሺህ ዓመታት ወሰዶበታል። ነገር ግን መቼ እንደሚሆን፡ ከመጀመሪያው፡ ያውቅ ነበር። ያውቅ ነበር፥ ሌላ ማንም አላወቀም። እርሱ ዝም ብሎ ይሆናል አለ። ሲሆን፡ ህዝቡ እንዴት ሊቀበለው እንዳለበት እስከማያውቅ ድረስ፡ በታላቅ ቅዤት ውስጥ ነበረ። ያው ነገር እንደገና አልተደገመም ብላችሁ ነው! ሁልጊዜ ይደገማል፡ ፈጽሞ አይወድቅም፡ በሁለቱም በኩል፡ ሁልጊዜ።

115 በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ምን አደረገ? የእርሱን መምጣት ጥላዎች አሳየ።

116 በዮሴፍ ህይወት አሳየው። የዮሴፍን ህይወት ብትመለከቱ፥ በወንድሞቹ የተጠላ፡ በአባቱ የተወደደ ነበር። ለምን? መንፈሳዊ ስለነበር፡ ራእዮችን ያይ ስለነበር ነው። ሌሎቹ ራእዮችን አላዩም፥ ፓትርያርኮች ነበሩ ዳሩ ግን ራእዮችን አላዩም፡ ህልሞችንም አልፈቱም። ዳሩ ግን በእርሱ ቀንተውበት ነበር። ለሰላሳ ብር ሊሸጥ ምንም አልቀረውም፡ ሊገደል ከተጣለበት ጉድጓድ ወጥቶ፡ በፈርዖን ቀኝ ተቀመጠ። ከዙፋኑ ሲወጣም፡ “ጉልበት ሁሉ ይንበርከክ፥ ዮሴፍ እየመጣ ነው፡” የሚል መለከት ይነፋል!

117 ልክ ኢየሱስ ያደረገውን ነው፡ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል። ዙፋኑን ለቆ ሲመጣ፡ እነሆ መለከት ይነፋል። ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል፡ ኢየሱስ ክርስቶስም፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ይመሰክራል። በትክክል።

118 ይህንንም በዳዊት ምሳሌ አሳይቷል፡ ተራራ ላይ ሆኖ ኢየሩሳሌምን እያየ... የተጠላው ንጉሥ፡ እያለቀሰ ነበር። “ዶሮ ጫጩቶቿን እንደምትሰበስብ፡ ልሰበስባችሁ ስንት ጊዜ ፈለግሁ፡ እናንተ ግን አልወደዳችሁም።”

119 በዘመናት ሁሉ፡ አንድ ቀን የመጨረሻው ጥላ እንደሚፈጸምና፡ የተሰፋ ቃሉ መሲሕ፡ ሙሉ በሙሉ እንደሚገለጥ እያወቀ በጥላዎች አሳየው። ሙሉው የተሰፋ ቃል ሲመጣም፡ ምንም እንኳን እርሱ በጥላ ቢያሳየውም... ከቀን ወደ ቀን፡ ከዓመት ወደ ዓመት፡ በጥላ አሳየው። እውነታው ሲመጣም ግን፡ አላመኑትም።

120 ያንኑ አድርጓል፡ በጥላ አሳይቷል፡ በቤተክርስቲያን ዘመናትና፡ በሁሉም ነገር፡ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ አሳይቶታል፡ ሰዎች ግን በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ናቸው፡ ሊረዱት የቻሉ አይመስልም። እንዴት የሚያሳዝን ነገር ነው!

121 እዚህ ውጭ እንደምናየው ወጣት፡ ግዙፍና፡ ጥሩ-ቁመና ያለው ወንድ፡ ሴቶች እንደሚያደርጉት፡ ፀጉሩን እንደ ሴቶች የተሠራ፡ ሰውነት ላይ ጥብቅ የሚል ሱሪ ያደረገ፡ እና ረጅም ሹራብ አንጠልጥሎ፡ ሐምራዊ ጫማ የተጫማ ወጣት ወንድ ማየት የተለመደ ሆኗል። ይህ ወንድነት ነውን? ኧረ፡ ጉድ ነው፡ እንዲህ ዓይነቱን ግለሰብ ወንድ ብሎ መጥራት! እጅግ ዘግናኝ ነገር ነው! በትክክል።

122 ያማረችና ተወዳጅ መሆን ሲገባት፡ የወንዶች ሱሪ አድርጋ፡ አፏ ውስጥ ሲጋራ ይዛ፡ ፀጉሯን ተቆርጣ፡ የምትወጣ ሴት ታያላችሁ። ሴትን እንዲህ ብሎ መጥራት እንዴት ያለ ነገር ነው! ኢየሱስ ማርያምን አላት፡ "አንቺ ሴት።" እንደዚያም መባል አልነበረባትም፥ እንስት መባል ነበረባት።

123 ዘመኑን፡ አስተውሉ! ለምን? አንዳንድ ጊዜ ቅን እንደሆኑ የሚናገሩና የሚያስቡ ሰዎች፡ ነገር ግን ድቅድቅ ጨለማ በዚህ ውስጥ አስገብቷቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚያ ይሆናሉ ብሏል። ኢሳይያስ 6ን አንብቡና በመጨረሻዎቹ ቀናት ሴቶች እንደዚያ ማድረግ ይገባቸዋል ወይስ አይገባቸውም የሚለውን ፈልጉ፡ ልክ መጽሐፍ ቅዱስ ይሆናሉ ያለው ነው የሆነው። የእግዚአብሔር ቃል ነው። መጨረሻውን ከመጀመሪያው ሰላዩ፡ ኤርምያስና ሌሎች የተለያዩ ነቢያት አሁን ስለምንኖርበት ስለዚህ ዘመን ተናግረዋል። ስለዚህ እነዚህን ነገሮች፡ በህዝቡ ላይ ያለውን ድቅድቅ ጨለማ እናያለን።

124 አዎ፡ ጥላዎችን በማሳየት፡ እግዚአብሔርን... በሺዎች የሚቆጠሩ ዓመታት ወሰዶበታል፡ በመጨረሻም እርሱ ሲመጣ አላወቁትም፡ ምንም እንኳ በዮሴፍና በዳዊትና በኤልያስና፡ እዚያ ታች ባሉት ሁሉ የተገለጠ ቢሆንም አላወቁትም። በእነርሱ ውስጥ ተገልጦ ነበር፡ ሆኖም ለምን ሊያዩት እንዳልቻሉ ልንረዳ አንችልም። እዚያው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ እርሱ የሚወለደው፡ "ከይሁዳ ቤተልሔም" እንደሆነ፡ ተጽፎ ነበረ። እንዴት ከድንግል፡ እንደሚወለድ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኘዋለን። "ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች፡ ሰሙንም አማኑኤል ይሉታል።"

125 ለምን ገደሉት? "ራሱን አምላክ ሰላደረገ፡" እርሱም አምላክ ነበር። እርግጥ ነው፡ ያምኑበታል። "ራሱን አምላክ ያደርጋል፡ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ያደርጋል፡ 'እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ፡' ይላል አሉ።" ለምን፡ እርሱ ነበር!

126 መጽሐፍ ቅዱስ፡ እርሱ "ድንቅ፡ መካሪ፡ የሰላም አለቃ፡ ኃያል አምላክ፡ የዘላለም አባት" ተብሎ ሊጠራ እንደሚገባ ይናገራል! እርሱም ያው ነበር። ያንን ለምን አልተረዱም?

"መጻሕፍትን መመርመር አለባችሁ፡" ማለቱ ምንም አያስደንቅም።

እነርሱም፡ "እኛ የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን" አሉ።

127 እርሱም፡ "የሙሴ ደቀ መዛሙርት ብትሆኑ ኖሮ፡ እኔን ታውቁኝ ነበር። ሙሴ ስለ እኔ ጽፏልና" አላቸው። እነርሱም አላወቁትም።

128 ደስ ከሚለው ከኢየሱስ ይልቅ፡ ወደ የሐይማኖት መግለጫዎቻቸውና ወደ የመሳሰሉት የሚሄዱበት ሰዓት፡ ዳግም በሰዎች ላይ መጥቷል። በትክክል። እነዚህ ታላላቅ ነገሮች እየመጡ ነው፡ ወደባሰ ጨለማና ወደባሰ ጨለማም እየከተቷቸው ነው። እግዚአብሔርም በቃሉ፡ በሰማያት ባሉ ምልክቶችና ድንቆች እየገለጠው ነው፡ ልክ በዘመኑና በደቂቃው ምን እንደሚሆን እየተናገረ ነው፡ ምን እንደሚሆን፡ እያሳየ ነው። እነርሱ ግን አሁንም በዚያው መንገድ መጓዛቸውን ይቀጥላሉ። ምንም ማድረግ የማይችሉ ይመስላሉ። ጥሩ ሰዎች፡ አዎን፡ ወዳጄ፡ ያኔ እንዳደረጉት አሁንም ያንኑ እያደረጉ ነው።

129 እኛ የጊዜ ፍጥረታት ነን። እግዚአብሔር የዘላለም ፈጣሪ... እግዚአብሔር ዘላለምን የፈጠረ ነው። እርሱ ጅማሬ የሌለው እና ማለቂያም የሌለው ነው። ታዲያ ለምን ራሳችሁን ለእርሱ አትሰጡም? ወደላይ ተመልከቱ፡ ዛሬ እያበራ ባለው የእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ደስታም አብሩ። ወዳጆች ሆይ፡ ሰዎች ለምን ያንን ማየት አቃታቸው?

130 አዳምጡ፡ እኔ ወንድማችሁ ነኝ። እወዳችኋለሁ። ዝም ብዬ ብታገስ፡ እንዲሁ፡ ዝምብዬ በመቀጠል፡ "ኦህ፡ ደህና፡ በዚህ ላይ እስማማለሁ፡ በዚህ-... "? እኔ ከእንደዚያ ዓይነት ነገር አልተሰራሁም። አይ፡ ወዳጄ። ቃል ከሆነ፡ ቃል ነው። እውነት ለሆነው ነገር እንድንቆም እግዚአብሔር ይርዳን! አዎን፡ ወዳጄ። ጥሩ ይሆን ነበር፡ እርግጥ ነው፡ የተሻለ አድናቆትም ባገኛችሁ ነበር። ዳሩ ግን፡ ያ ቀን ሲመጣ እነዚያ በአጥንት የተሞሉ ጣቶች ፊቴ ላይ ተጠቁመው፡ "የተሻለውን ታውቅ ነበር፡ ነገር ግን ልትነግረን አልቻልክም" ሲሉኝ እዚያ ቆሜ ምን አደርጋለሁ? ፊው! አይ!

131 እንደ ጳውሎስ እሆናለሁ፡ "የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ከመናገር ወደኋላ አላልኩም።" የማንም ሰው ደም በእኔ ላይ የለም። በፈለገው ቦታ ይሂድ። እውነት ነው። እግዚአብሔር ያውቀዋል፡ ይደግፈዋልም እውነት መሆኑንም ይናገራል።

132 ወደ ምን ልመለስ፡ ወደ ወንድም ብራንሐም? እናንተ፡ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ብታደርጉ ሞኞች ትሆናላችሁ። ወደ ክርስቶስ ተመለሱ፡ እርሱም ቃል ነው! ወደ ክርስቶስ ተመለሱ!

133 ከየሐይማኖት መግለጫዎች ራቁ! ተመለሱ... እኔ ግድ የለኝም፡ የእናንተን የሐይማኖት መግለጫ የጀመራችሁት፡ ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ሊሆን ይችላል፡ ይህም ዝም ብላችሁ... ያ ለእግዚአብሔር አንድም ትርጉም አይሰጠውም። እነዚያ ሰዱቃውያንና ፈሪሳውያን ከእናንተ ከረጅም ጊዜ በፊት ጀምረው ነበር፡ ተኮነኑ።

134 ኦህ፡ የመንፈስ ቅዱስን ማስረጃችሁን በተለያዩ ድርጊቶች ላይ ለማስቀመጥ ትሞክራላችሁ። በመንፈስ ቅዱስ መገለጦች አምናለሁ። ምን ያደርጋል? ጴንጤቆስጤዎች፡ "በልሳኖች መናገር የመንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያ ማስረጃ ነው" ይላሉ። ጠንቋዮችና አስማተኞች በልሳን ሲናገሩ አይቻለሁ። በልሳን ሲናገሩና ከሰው የራስ ቅል ውስጥ ደም ሲጠጡ፡ ትንቢት ሲናገሩና እግዚአብሔር የሚባል ነገር መኖሩን ሲክዱ አይቻለሁ። እርሳስ በጠረጴዛ ላይ አስቀምጠው ወደ-ላይና-ወደ ታች እንዲዘል በሚያደርጉበት፡ በማይታወቅ ልሳን በሚፅፉበትና በሚተረጉሙበት የጠንቋዮች ሰፈር ውስጥ ሆኜ አውቃለሁ። በትክክል። ያ ከዚህ ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም... ቢሆንም፡ እግዚአብሔር በህዝቡ በኩል በማይታወቅ ልሳን እንደሚናገር አምናለሁ። እናንተ ግን በእርሱ ላይ በጣም ብዙ ጫና ታደርጋላችሁ፡ "ለምን አስተርጓሚ ያስፈልጋል? ለምን ለቤተክርስቲያን የሚሆን መልዕክት መሆን አለበት? "

135 ከዚያም እናንተ ሌሎቻችሁ፡ እንዲህ ትላላችሁ፡ "የመንፈስ ፍሬዎች፡ የምናውቀው በዚያ ነው። ፍቅር፡ ደስታ፡ ማስረጃውን ያገኘነው በዚህ ነው" ትላላችሁ። እንደዚያ ነው? ከሆነ ክርስቲያን ሳይንስ ሁላችሁንም

በልጧችኋል። እናንተ ጴንጤቆስጤዎች፡ ሜቶዲስቶችና፡ ባፕቲስቶች፡ ተደምራችሁ ከምታደርጉት ይልቅ እነርሱ ያንን በብዛት ያደርጉታል።

136 ምን እንደሚሆን ተመልከቱ። የመንፈስን ፍሬዎች ላሳያችሁ፡ ከዚያም በኋላ በዚያ መሄድ ትችሉ እንደሆነ ተመልከቱ። ኢየሱስን እንመልከት። ስለምናገረው ቃል እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝ፥ ላሳያችሁ ስል ለአንድ ደቂቃ ያህል፡ ከእርሱ ጋር ልቃረን፡ ይህን የሰዎች ካውንሰል እዚህ ውሰዱ፡ ይህንንም የሰዎች ካውንሰል ዛሬ ከሰዓት በኋላ ውሰዱ። ይህንን እላለሁ...

137 "ጌቶች ሆይ፡ እዚህ አካባቢ የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚባል፡ አንድ ወጣት አለ፡ ከእርሱ ጋር ምንም አትገናኙ! የመጀመሪያው ማን ነበር... መጽሐፍ ቅዱሳችን ምን ያስተምረናል? እግዚአብሔር ፍቅር ነው። ስትወለዱ ከአጠገባችሁ የቆመው የመጀመሪያው ሰው ማን ነበር? ያ ሩህሩህ አዛውንት፡ ካህናችሁ ነው። በትክክል። በችግር ውስጥ በነበራችሁበት ጊዜ ወደ እናንተ የመጣው፡ ምንም ገንዘብ በሌላችሁ ጊዜ፡ ገንዘብ ያበደራችሁ ማን ነበር? ያ ሩህሩህ አዛውንት፡ ካህናችሁ። በትክክል። ለመለያየት ተቃርባችሁ በነበረ ጊዜ፡ በእናንተ ትከሻና በእናታችሁ ትከሻ ላይ እጁን ጭኖ፡ ፀልዮ ወደ እግዚአብሔር የመለሳችሁ ማን ነበር? ያ ሩህሩህ አዛውንት፡ ካህናችሁ። እናንተና ጎረቤታችሁ በጠብ ውስጥ በነበራችሁበት ጊዜ፡ ወደ እናንተ ወገን ሆኖ፡ ወደ ህብረት የመለሳችሁ ማን ነበር? ያ ሩህሩህ አዛውንት፡ ካህናችሁ። በትክክል። እዚያ ማዶ ባለው ቀን በእናንተ ላይ የመጨረሻውን ቃል የሚናገረው፡ ማን ነው? ማን ነው? እንድትበሰብሱ ሲቀብሯችሁ፥ ሩህሩህ አዛውንት፡ ካህናችሁ ግን መጥቶ ይባርካችኋል፡ የእግዚአብሔርንም ቃል ከእናንተ ጋር ይልካል። ያ ሩህሩህ አዛውንት፡ ካህናችሁ!

138 "ታዲያ፡ ስለዚሁ የናዝሬቱ ኢየሱስ ስለሚባለው ሰው ምን ትላላችሁ፡ አያችሁ፡ ከየትኛው ትምህርት ቤት ነው የመጣው? ያ ሩህሩህ አዛውንት፡ ካህናችሁ፡ ህይወቱን ሙሉ መሰዋዕት ያደርጋል። አያቱ ካህን ነበሩ። ቅድመ-ቅድመ-ቅድመ-ቅድመ-ቅድመ-አያቱ ካህን ነበረ። ሙሉ ጊዜውን በድርጅቱ ውስጥ አሳልፏል። በቃሉ ሰልጥኗል፥ ስለሚናገረው ነገር ያውቃል።"

139 አሁን የምንናገረው ስለ መንፈስ ፍሬዎች ነው፥ ቸርነት፡ ፍቅር፡ ደስታ፡ ሰላም፡ ማስተዋል፡ ትዕግስት፡ መታገስ፡ አያችሁ፡ የመንፈስ ፍሬ።

140 "ይህ ኢየሱስስ፡ ከየት ነው የመጣው? ከማንኛውም ትምህርት ቤት ስለመምጣቱ አንዲትም ቃል የለንም። እርሱ የሚያደርገው እኛ የገነባናቸውን ትምህርት ቤቶች ለማፍረስ መሞከር ብቻ ነው።" እዚያ ብዙ የመንፈስ ፍሬ የለም፡ አይደለም እንዴ?

141 "እነዚያ ምስኪን ነጋዴዎችና፡ የንግድ ሰዎች እዚያ በነበሩበት ቦታ ምን አደረገ... እነርሱ፡ በጎችን ስለማያረቡ፡ ስለዚህ ሰ—ሰውዬው በግ ማምጣት እንዲችል ትንሽ ጉረኖ እዚያ ውጭ አዘጋጁ። ያ ምስኪን ነጋዴ፡ እ—እርሱ የእግዚአብሔር መስፈርት ስለሆነ፡ በግ ማቅረብ ይፈልጋል። ስለ ነፍሱ ማቅረብ እንዲችል፡ ለነጋዴው ለመሸጥ፡ በ—በጉን ያመጣል። ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ምን አደረገ? ጠረጴዛዎቻቸውን ገለበጠባቸው፥ ጥቂት ቆዳ ወሰዶ ጎነጎነ፡ እነዚያን ካህናት ከዚያ እየደበደበ አስወጣቸው፥ ያንም ሩህሩህ አዛውንቱ፡ ካህናችሁን፡ 'ግብዝ፥ የሳር ውስጥ እባብ' አለው!"

142 አሁን ያንን የመንፈስ ፍሬ ትሉታላችሁ? ፈጽሞ አትሉም። ታዲያ የመንፈስ ፍሬያችሁ የት ላይ ነው የሚያርፈው? ከምታስቡት በላይ እጅግ ርኅሩኅ ከመሆኑ የተነሣ፡ በብዙ ህዝብ መካከል ሲያልፍ፡ ብዙ ሰዎች፡ አይነ ስውራን፡ ሽባዎች፡ የተጎዱ፡ የሰለሉ፡ አንካሶች፡ ወድቀው ሳሉ፡ አንዳቸውንም ሳይፈውስ ሲያልፍ፥ በርህራሄ ተሞልቶ ነበር። ስጋዊ አዕምሮ ያላቸው ሰዎች ያንን ፈጽሞ አያውቁትም። የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች አያስተምሩትም። እርሱ መገለጥ ነው። በእርግጠኝነት። የመንፈስ ፍሬ እዚያ ላይ ይወድቃል፡ አይደለም እንዴ? እነዚያ ካህናት አስር እጥፍ የመንፈስ ፍሬ ነበራቸው።

143 ትክክል የሆነውን ነገር እንዴት ታውቃላችሁ? የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ፡ የዘመኑ ብርሃን ነው። በእርግጠኝነት። የእግዚአብሔርን ቃል ሲገለጥ ማመን፡ የመንፈስ ቅዱስ ማስረጃ ያለው እዚያ ላይ ነው። የተገለጠው ቃል፡ እርሱ ነበር። አንዳንዶቹም ካዱት፡ ሳቁበት፡ አሾፉበት ጠ—ጠንቋይ ብለው ተሳለቁበት፡ የሆነ ክፉ መንፈስ ብለው ጠሩት፥ እዚያ ላይ ማስረጃ አለ፡ በልሳኖች መናገር፡ የፍሬዎች ማስረጃ እዚያ ጋር ነው። ያለው ብቸኛ ማስረጃ፡ ሰዎች የተፃፈውን ቃል ሲያምኑ ነው። ሲጸና፡ በብርሃኑ ውስጥ ተመላለሱ። ለዘመኑ ተሰፋ የተሰጠው ቃል እርሱ ስለነበረ የዘመኑ ብርሃን ኢየሱስ ነበር፡ ለነርሱም ያንን ለመንገር ሞከረ፡ ነገር ግን እነርሱ ያንን ለመረዳት በጨለማ ውስጥ በ—በጣም ገብተው ነበር። አሁንም፡ ዛሬም፡ እንደዚሁ ነው።

144 አሁን እኛ፡ የዘመኑ ፍጥረታት ነን። መንገዳችሁን ለእርሱ ሰጡ፡ እርሱም የወደፊቱን ያቃናልናል፡ ምክንያቱም በቃሉ ውስጥ እንዳለ ሆኖ እናየዋለንና።

145 የዛሬውን የተሰፋ ቃል ሲያጸናው አይታችኋል። በጨረቃ ላይ ባሉት ምልክቶች ታዩታላችሁ። በቤተክርስቲያናት ውስጥ ታዩታላችሁ። አስታውሱ።

146 "አንተ፡ 'በቤተክርስቲያን ውስጥ' አልህ፡ ያ ከቤተክርስቲያን ጋር ምን የሚያገናኘው ነገር አለው" ትላላችሁ?

147 አንድ አፍታ ቆዩ። ጨረቃ ቤተክርስቲያንን ትወክላለች። ኢየሩሳሌም በዓለም ላይ ከሚታወቁ የቤተክርስቲያን ከተሞች ሁሉ አንጋፋዋ ናት። መልከጼዴቅ ከዚያች ከተማ መጣ፥ የሳሌም ንጉስ፡ የሰላም ንጉስ፡ የኢየሩሳሌም ንጉስ። በትክክል፡ በዓለም ላይ አንጋፋዋ ከተማ ናት። ህግ እንደተመሰረተበት ቦታ፡ ያች ጨረቃ ነበረች፡ አሁን ደግሞ ይህ የአህዛብ የጨለማ ማዕበል በእርሷ ላይ እየመጣ ነው። እርሱም፡ "የ—የአህዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ቤተክርስቲያን የኢየሩሳሌምን ቅጥር ትረግጣለች" አለ። አሁን እነሆ እሷ። እየኖርን ያለነው ልክ በእርሱ ውስጥ ነው። ሰሜ ዊሊያም ብራንሃም መሆኑ እርግጠኛ እንደሆነ ሁሉ፡ እርሷም ወደዚያው ትመለሳለች። አዎን፡ ወዳጄ፡ ልናየው እንችላለን። እርሷ ጥላ ሆናለች፡ ጥላዋ ታይቷል፡ አስቀድሞ ተነግሯል፥ የተመረጡትን እየጠራ ነው። ሌሎቹ፡ በመንገዳቸው ሲጓዙ፡ ዝም ብለው በጨለማ ውስጥ ይዳብሳሉ። መልካም።

148 አሁን ቃሉ ጸንቶ እናየዋለን። እናምናለን። ስለዚህ እርሱ የዘመኑን ቃል፡ ምን እንደሆነ ካጸናው፡ ዓመቱ ስለሚያመጣው ነገር ምን ያሳስበኛል? ስለሚቀጥለው ዓመት ምን ያሳስበኛል? ዛሬ ብኖር ወይም ዛሬ ብሞት ምን አገባኝ? ተሰፋ የሰጠው ቃል ሁሉ ይጸናል፡ እያንዳንዱ! ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ተሰፋ ከሰጠ በኋላ፡ ዛሬ ያንን ማድረግ ከቻለ፥ መቶ ሺህ ዓመታት

ቢሆንም እንኳ፡ ቤተክርስቲያንን፡ የተቤዠችውን፡ ሙሽራይቱን፡ ወ—ወስዶ ከዚህ ለማውጣት፡ ኢየሱስ ዛሬ በሚታይ አካል፡ ወደ ምድር ይመለሳል። ምንም ቢመጣ፡ ቢሄድ፡ ፋሽኖች፡ "ቀጥሉ" ቢሉ፡ ሰዎችም በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ መዳዛቸውን ቢቀጥሉና ማመን የፈለጉትን ቢያምኑም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ዳግመኛ ይመለሳል። እንግዲያውስ፡ የወደፊቱን በእርሱ እታመናለሁ። "ጌታ አምላክ ሆይ፡ ነገ ምን እንደያዘ ባላውቅም፡ ነገን አንተ እንደያዝከው ግን አውቃለሁ።"

149 ቃሉ ልክ እንደ ታላቅ ሲምፎኒ ነው። ከእናንተ ውስጥ ስንቶቻችሁ ሲምፎኒ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እሺ፡ ሁሉም ሰው። አሁን አስታውሱ፡ ሲምፎኒ ማለት ሙዚቃ በድራማ ውስጥ ሲጫወት ነው። ያ በትክክል የገባኝ ይመስለኛል፡ ሲምፎኒ። "ጴጥሮስና ተኩላው፡" ያንን የድሮ ታሪክ ታስታውሳላችሁ፡ እንዴት ያደርጉ እንደነበረ... ያንን ሰምቻለሁ፡ ድራሞችን ወስደው ዉድፔከር የተባለው ወፍ በ—በማንቁርቱ የሚያወጣውን አይነት ድምጽ በማውጣት፡ ጴጥሮስ ሲወጣ፡ የተኩላ ድምጽ አይነትና፡ የቀንደ መለከት መነፋት፥ ሲምፎኒ።

150 አሁን፡ ሲምፎኒን ካልተረዳችሁት፡ ምንም ትርጉም የሌለው ጫጫታ ይሆንባችኋል፡ ካልተረዳችሁት እንደዚያ ነው። ምን እንደሆነ መረዳት አለባችሁ። ሁሉም የሚደረገው በምልክቶችና በእንቅስቃሴዎች ነው፡ ነገር ግን በዚህ ሲምፎኒ ውስጥ ድራማን ይሰራል። አሁን፡ ሲምፎኒን የሚረዳው ብቸኛው ሰው፡ አቀናባሪውና እርሱን ለማወቅ ፍላጎት ያላቸው ብቻ እንደሆኑ እናስተውላለን፡ ለውጦቹን ያውቃል፡ ምን እንደሚፈጠር ያውቃል።

151 አቀናባሪው እያንዳንዱን እንቅስቃሴ፡ ከመጨረሻው እስከ መጀመሪያው፡ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ያውቃል። ያንን ታውቃላችሁ? የፃፈው ሰው፡ ይህንን ያቀናብራል፡ እያንዳንዱን ትንሽ መጋጠሚያ ያውቃል። እያንዳንዱን መጋጠሚያ የሚያውቅ ከሆነ፡ ዳይሬክተሩም ለመምራት፡ ያንኑ ማድረግ አለበት። አሁን በእርሱ ውስጥ የእናንተን የሐይማኖት መግለጫ እንዴት ልታስገቡት ነው? አንድ የዚያች በትር ትንሽ ስህተት፡ የዚያ ምልክት፡ በመጋጠሚያ ላይ አንዳች ትንሽ የተሳሳተ-ምልክት፡ መላውን ኦርኬስትራ ያበላሸዋል፡ መላውን ሲምፎኒ ያበላሸዋል። አሁን ያ እውነት መሆኑን ታውቃላችሁ። አቀናባሪውና ዳይሬክተሩ በአንድ መንፈስ ውስጥ መሆን አለባቸው።

152 ለዚህም ነው አገልጋዩና የእግዚአብሔር ቃል፡ ከዘመን መባቻ ጀምሮ እግዚአብሔር ሲጫወተው የነበረው ታላቁ ሲምፎኒው ነው፥ አገልጋዩ፡ ከቃሉ ጋር ሆኖ፡ ወደዚህና ወደዚያ እያየ እንዲህ ማለት የለበትም፡ "**ይህ** ሊሆን ይገባል ብዬ እምናለሁ፥ እናንተ **በዚህ** መንገድ ልታደርጉት ይገባችኋል።" የሙዚቃው ኖታ እንደሚለው መሄድ አለበት። ወንጌል መሰበክ ያለበት በዚያ መንገድ ነው፡ ቃሉ ውስዱት በሚለው መንገድ መሆን አለበት። ታውቃላችሁ፡ በዚያ ውስጥ አንድ የሐይማኖት መግለጫ ብታስገቡ፡ ሙሉ ነገሩን ታበላሹታላችሁ። ድራማውን ለመስራት ልክ በትክክል መሄድ አለበት።

153 ዳይሬክተሩ አቀናባሪው ባለው መንገድ መሄድ አለበት፡ ሙዚቃውን፡ በትክክል መምታት አለበት። አሁን ተመልከቱ፡ ሁሉም በምልክቶች ነው የሚደረገው፡ ትክክለኛውን ድምጽ ለመስጠትም፡ ትክክለኛው ዓይነት ምልክት መሆን አለበት።

154 ጳውሎስ፡ “መለከት የማይታወቅን ድምጽ ቢሰጥ፡ ለጦርነት ማን ይዘጋጃል” አለ?

155 አሁን መጽሐፍ ቅዱስን የፃፈውን አቀናባሪውን፡ እግዚአብሔርን፡ እዩት፡ ሙሉ በሙሉ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው። የዘመንን ለውጦች ያውቅ ነበር። ሰውዬው፡ እ—እነርሱን የሚመራው ዳይሬክተር፡ የዘመኑ ምልክት፡ ልክ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምልክቶች ጋር አብሮ መሄድ አለበት። ሃሌሉያ! ማይ፡ ማይ፡ ማይ፡ ማይ፡ ማይ!

156 ኦህ፡ ወንድሜ፡ እህቴ፡ የዓለም ችግር ምንድነው? ለምንድነው እኔ ያበድኩት? የትም ቦታ ቢሆን የተሳሳተ ነገር አለ። ሲምፎኒው ከሙዚቃው ኖታ ጋር አልተሰማማም! ሊሰበክ ሊገለጥ የሚገባው ቃል ሲሆን፡ እነርሱ የቤተክርስቲያን የሐይማኖት መግለጫንና፡ ሌላውን ነገር ሁሉ እያደረጉ ነው። በዳይሬክተሮቹ ላይ የተበላሸ ነገር አለ፡ ከዚያም ሙሉው ቡድን ይደባለቃል፡ ምን ማድረግ እንዳለባቸውም አያውቁም። ሁሉም ግራ ተጋብተዋል፡ “ምን ተፈጠረ? **ይህ** ምን አደረገ? **ይህ**፡ ምን ሆነ? **ይህ**፡ ያ እንዴት ሆነ? አሁን ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም። ይበተናሉ፡ ምክንያቱም ከቃሉ ጋር ፈጽሞ አልተሰማማምና። የመጨረሻ-ዘመን ሪቫይቫል፡ ብለን ከምንጠራው፡ ጋር ያለው ችግር ያ ነው። የጴንጤቆስጤ መልእክታችን ችግር ያ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ መሰመር ስተናል፡ ሄደን ልክ እነርሱ ያኔ እንዳደረጉት ተደራጀን። መሰመር ስታለች።

157 እግዚአብሔር ሆይ፡ ማረን። ይህንን እንዳለ ማሰረፅ የምችልባቸው፡ ማዳረስና ማፍሰስ የምችልባቸው፡ ቃላት በኖሩኝ ምኞቴ ነው።

158 ወንድሜ፡ እህቴ፡ አይታያችሁምን፡ መሰማማት አለበት? ዳይሬክተሩ ከቃሉ ጋር መሆን አለበት። እርሱ አንዱን ነገር ሲናገር፡ ሌላ ነገር አትናገሩ፥ የተሳሳተ ምልክት ይሰጣል፡ ከዚያም ሙሉ ነገሩ ከምት ይወጣል። በትክክል። የእግዚአብሔር ቃል ታላቅ ሲምፓኒ፡ ማለትም፡ ሲምፎኒ ነው። ይቅርታ አድርጉልኝ። በሙዚቃው ውስጥ ልክ እርሱ እንደጀመረው፡ መጀመር አለባችሁ። ከእርሱ ጋር መጀመር አለባችሁ። አስተውሉ፡ ወደ ምቱ ውስጥ ግቡ።

159 “ደህና፡ ቤተክርስቲያን ተቀላቅያለሁ፡” ትላላችሁ። ያ ቃናው አይደለም። “እንዲህ አድርጌያለሁ።” ያ ቃናው አይደለም። “ወደ መሠዊያው ሄጄ ‘ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ፡’ ብ—ብያለሁ።” ሰይጣንም ያንኑ ያደርጋል። ያ ቃናው አይደለም። እያችሁ፡ ከሰልት ትወጣላችሁ። ምን ተፈጠረ? ምናልባት አንድ ዳይሬክተር፡ “እጅ ተጨባበጡና ስማችሁን በመዝገቡ ላይ ፃፉ፥ ክለባችንን፡ ድርጅታችንን ተቀላቀሉ” ብሏችሁ ይሆናል። ሙሉ በሙሉ ከምቱ ውጭ ናችሁ!

160 ከዚያም እውነተኛው ነገር እዚህ ውጭ ባለው ትንሽ ቡድን ውስጥ መሆን ሲጀምር፥ እንዲህ ትላላችሁ፡ “ደህና፡ **ስለዚያስ**፡ እነርሱ ከሰምምነት ውጭ ናቸው” ትላላችሁ። ወደ ቃሉ ተመልሳችሁ ከሰምምነት ውጭ የሆነው ማን እንደሆነ ተመልከቱ። እግዚአብሔር ተሰፋ የሰጠውን ተመልከቱ። አቀናባሪው ስለእርሱ የተናገረውን ተመልከቱ።

161 እያችሁ፡ በጉባኤያችሁ ውስጥ ሁሉም ሰው አላችሁ። ዓለም ዙሪያውን የሚመለከተው ለዚህ ነው። ቤተክርስቲያን እንደ ብሩህ፡ የምታበራ ኮከብ፡ ማንም ሊያደበዝዛት፡ ማንም ሊኮንናት በማይችል ተራራ ላይ እንደተቀመጠች፡ ብርሃን ሆና መታየት ሲገባት እንደዛ ታደርጋለች።

162 እናም፡ ዛሬ፡ የዓለም መሳቂያ ሆናለች፡ ምክንያቱም ዳይሬክተሮቹ ከአቀናባሪው ጋር እንዳትስማማ አድርገዋታልና። ምን ማለቴ እንደሆነ እያችሁ? በዚያ ውስጥ የሌሎትን ነገሮች እየተጫወቱ ነው። ሙዚቀኞቹ አሁን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ብዙም አያውቁም፥ ቤተክርስቲያን፡ ሁሉም በውዥንብር ውስጥ ናቸው። ስለዚህ ሁሉ ነገር፡ ለዓመታት ሁሉ ስንነጋገርና፡ ስንኮንነው ቆይተናል፡ አሁን ደግሞ ልክ አብረነው እየተቀላቀልን ነው። ኦህ፡ የሆነ ቦታ የሆነ የተሳሳተ ነገር አለ።

163 አስተውሉ፡ በሙዚቃው ውስጥ ልክ እርሱ እንዳደረገው መጀመር አለባችሁ፡ ወደ ምቱ ውስጥ ግቡ፡ ወደ ተሰፋ ቃሉ ውስጥ ግቡ። በመጀመሪያው እንዴት እንዳደረገው ተመልከቱ፡ በመካከለኛው ዘመን እንዴት እንዳደረገው ተመልከቱ፡ አሁን እንዴት እንደሚያደርገው ተመልከቱ፡ ሁልጊዜ ያው ነው።

164 ዳይሬክተሩን፡ እንዴት እንደሚያደርገው ተመልከቱ። ካላደረገው፡ ወደ አንድ ድርጅት የሚጠቁማችሁ ከሆነ፥ እንዲህ ያደረገ ዳይሬክተር ፈጽሞ አልነበረም። ዳይሬክተር ሁልጊዜም የሚያመለክታችሁ ወደ ቃሉ ነበር። የቀድሞዎቹ ነቢያት፡ ወደ ቃሉ አመለከቱ። እነርሱ ቃል ነበሩ። ቃሉን ኖሩ። ምንስ አደረገ? እግዚአብሔርን ገለጠ። ያ ለዚያ ዘመን የተፃፈውን ቃል ህያው አደረገው፡ ምክንያቱም ወደ እነርሱ መጥቷልና። ለእነርሱ ተገልጦ ነበር። ያ አለታቸው ነበር። ሃሌሉያ!

165 ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ የእኛ አለት ነው። የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል፡ "በዚህ አለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሰራለሁ።" ለእውነተኛው እማኝ፡ ሻሎም። ሰላም! በመጨረሻው ዘመን ላይ ነን። የቃሉ መገለጥ፡ "በዚህ አለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሰራለሁ" የሚል ነው።

166 አንዱ፡ "ደህና፡ አንተ ታላቅ ሰው ነህ። አንተ እንደ ሙሴ ነህ። አንተ ታላቅ ሰው ነህ። አንተ እንደ... " ያ አይደለም።

ነገር ግን መገለጡ፡ "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" አለ።

167 እንዲህ አለ፡ "ይህንን በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ፡ ሰጋና ደም አልገለጠልህም። በዚህ በተገለጠው እውነት ላይ፡ ቤተክርስቲያኔን እሰራለሁ" አለ።

168 ምንድነው? እርሱ ቃል ነው። "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡" ቃሉ አሁንም እግዚአብሔር ነው። ልክ እርሱ፡ ዛሬም ያው ነው፡ እንደነበረው ራሱን ይገልጣል፥ ሙሴና ኤልያስ፡ ወደታች፡ ኢየሱስ፡ ዛሬም ያው አምላክ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው" ያደርገዋል፡ ዕብራውያን 13፡8። እያችሁ፡ ፈጽሞ ወደ አንድ ቡድን አላመለከቷችሁም። ያመለከቷችሁ ወደ አንድ አካል ነው፡ ያመለከቷችሁ ወደ ቃል፡ ወደ እግዚአብሔር ነው።

"ከዬት ነው የምጀምረው፡ ወንድም ብራንሃም? "

169 በመስቀሉ ላይ፡ በመስቀሉ ላይ ከእርሱ ጋር ጀምሩ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ያንን ነው፡ “ንስሐ ግቡ፡ ቃሉን እመኑ።” ከዚያም በተቀረው የቃሉ ምት ውስጥ ቀጥሉ።

እናንተም፡ “ደህና፡ ምን ላድርግ” ትላላችሁ?

170 የቃሉን ምት መከተላችሁን ዝም ብላችሁ ቀጥሉ። በማመን ውስጥ የመጀመሪያው ነገር **ንስሐ** መግባት ከሆነ፡ ያንን አድርጉ፡ ያ የመጀመሪያው እርምጃችሁ ነው። ቀጣዩን እርምጃችሁን ቃሉ በሚለው ቦታ ላይ አድርጉ። ወደፊት፡ ወደፊትና ወደፊት፡ ከእርሱ ጋር መጓዛችሁን ቀጥሉ።

171 የእግዚአብሔር ሲምፎኒ አካል ከሆናችሁ ምቱን አታቋርጡ። የቃሉን ምት አታቋርጡ። እንዲህ ብላችሁ አትጠይቁ፡ “ደህና፡ ለምን? **ይህ** ለምን ሆነ? ወንድም ብራንሃም፡ ሞክሬው ነበር፡ እነርሱ ሲያባርሩኝ፡ ምን እንዳደረግሁ ታውቃለህ? በቃ በረሃብ ልሞት ምንም አልቀረኝም።” ለምን ብላችሁ አትጠይቁ። እርሱ ምቱን፡ እንዴት መለወጥ እንዳለበትና፡ ምን መጋጠሚያዎችን ማድረግ እንዳለበት ያውቃል፡ አዎ፡ ወዳጄ፡ ተፅፏልና። ስለእርሱ ሁሉንም ያውቃል። ምቱን ያውቃል። ለምን ብላችሁ አትጠይቁ። እመኑት!

172 እግዚአብሔር በታሪክ ዘመን ሁሉ፥ በእያንዳንዱ ዘመን ውስጥ፡ በተስፋ ቃሉ ወርዷል፡ ወደ ተመረጡትና ወደ ጸኑት ሰዎች ሲመጣ፡ በእግዚአብሔር ኃይል ቃናው ፈጽሞ አላቋረጠም። በኖኅ ዘመን የነበረው የቃሉ ቃና፡ በኖኅ ዘመን የነበረው የቃሉ ቃና፡ በሙሴ ዘመን፡ በኤልያስ ዘመን፡ በዮሐንስ ዘመን፡ በዳዊት ዘመን፡ በኢየሱስ ዘመን፡ ወደታች፡ የቃሉን ቃና እንደጠበቀ ነው፡ በትክክል ወደታች፡ ፈጽሞ አላቋረጠውም። በታሪክ ውስጥ በትክክል መጥቷል። ያዩትና ያመኑት፡ የተመረጡት ዘርም፡ በትክክል ወደዚያው ምት ውስጥ አብረውት ይገባሉ።

173 ሌሎቹ እንዲህ ይላሉ፡ “ደህና፡ ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን የምትለው... ” ያ ከእርሱ ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለውም። ለዚያ አልተወለዳችሁም።

174 የተወለዳችሁት ወደ ቃሉ ነው፡ የተወለዳችሁት ወደ ክርስቶስ ነውና። ክርስቶስ ቃል ነው፡ አዎ፡ ወዳጄ፡ እያንዳንዳቸው በዘመናቸው።

175 እናንተም፡ “ደህና፡ ወንድም ብራንሃም፡ ልነግርህ የምችለው፡ ወደፊት መመልከት አልችልም” ትላላችሁ።

176 እንግዲያውስ ወደ ላይ ተመልከቱ። ወደላይ ብትመለከቱ፡ እንደምታዩት፡ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቷል፥ ሻሎም፡ ሰላም፡ የእግዚአብሔር ሰላም ያሳርፋችሁ።

177 እናንተም፡ “ታዲያ ሌሎቹ ለምን ያሾፉብኛል፡ ወንድም ብራንሃም? ታውቃለህ፡ ሌሎቹ ያሾፉብኛል፡ እ—እኔ ‘ረዥም ፀጉር’ እንዳለኝ፡ ለሴቶቹ ‘ኋላ ቀር’ እንደሆንኩ ይናገራሉ” ትላላችሁ። ወንዶቹም፡ “መጽሐፍ ቅዱስን ስለማምን፡ ‘ከእንግዲህ ከእኛ ጋር ህብረት የለህም። ያ—ያንን **እንዲህ-እና-እንዲህ** የሚባለውን ስለማመንህ ልንቀበልህ አንችልም’” ይላሉ።

178 ልክ ቃሉ እንደተፃፈው መሆኑን ታውቃላችሁ። ከዚያ እግዚአብሔር ያንን ሊደግፍላችሁ፡ ግዴታ አለበት። በእርግጠኝነት። ስለዚህ ለምን ያሾፋሉ የሚለው፡ አያስጨንቃችሁ። እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነው። አስታውሱ፡

ስለቃሉ መከራን መቀበል የፀጋው የእድገት ህመሞች ነው። ስለቃሉ መከራን ስትቀበሉ፡ ያ የእድገት ህመም ብቻ ነው።

179 የአሰር፡ የአሰራ ሁለት ዓመት፡ ትንሽ ልጅ፡ እንዴት ህመም እንደሚሰማው ታውቃላችሁ። ገብቶ፡ እንዲህ ይላል፡ "እማዬ፡ እጆቼ ያሙኛል እግሮቼም ያሙኛል፡" የመሳሰሉትን ይላል። የእድገት ህመሞች ናቸው። አንዳንድ ጥሩ ሻይታሚኖች እንዳሉት ያሳያል። እያደገ ነው።

180 አንድ ሰው በእናንተ ላይ ማሾፍ ሲጀምር፡ እንዲህ ሲል፡ "እርሷ ኋላ ቀር ናት። እርሱን ተመልከቱት፡ እርሱ... ኦህ፡ እነግራችኋለሁ፡ እርሱ በፊት" ሲል... መልካም፡ ዝም ብላችሁ አስታውሱ፡ እነዚህ የእድገት ህመሞች ናቸው። ያ መከራ ለእናንተ ጥሩ ነው። የእድገት ህመሞች ናቸው።

181 ኦህ፡ አዎን፡ መሰቀሎችንና መንታ መንገዶችንና መገናኛዎችን ይፈቅዳል። ለአገልግሎቱ እኛን ፍፁም ለማድረግ፡ ሁልጊዜ ያንን ያደርጋል። እነዚያ ነገሮች እንዲሆኑ ይፈቅዳል። ያንን ልትረዱት አትችሉምን? ያንን የሚያደርገው ለጠራችሁ ጥሪ ፍፁም ሊያደርጋችሁ ነው። ያ የእናንተ የእድገት ህመም ነው። ዳንኤልን እንደዚያ አድርጎታል፡ ታውቃላችሁ።

182 የዕብራውያንን ልጆች፡ በእቶን እሳት ውስጥ አድርጓቸዋል። የእቶኑ እሳት ምን አደረገ? የእቶኑ እሳት ያሰራቸውን ማሰሪያዎች ብቻ ነው የበጠሰው። እሳቱ ያደረገው ያንን ብቻ ነው፡ ማሰሪያዎቹን ብቻ ነው ያቃጠለው።

183 አንዳንድ ጊዜ የዓለምን ማሰሪያዎች ከእኛ ላይ ለመበጠስ፡ ከዓለም ሊያሰወጣችሁ የሚያስችሉ ፈተናዎች ያስፈልጋሉ። በመጀመሪያ፡ ከየሐይማኖት መግለጫችሁ ሊያወጣችሁ፡ ይገባል። በወንዝ ውስጥ እየሰመጠ እንዳለ ሰው፡ ውሃን ከሰውዬው ውስጥ ከማውጣታችሁ በፊት ሰውዬውን ከውኃው ውስጥ ማውጣት አለባችሁ። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ማድረግ ያለበት በዚያ መንገድ ነው። አንዴ፡ እንዲያባርሯችሁ ይተዋቸዋል፡ ከዚያም ዓለምን ከውስጣችሁ ያወጡታል። በመጀመሪያ፡ ከ—ከዓለም ሊያወጣችሁ ይገባዋል። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ የእድገት ህመሞች ናቸው ያንን የሚያደርጉት። ኦህ፡ አዎን።

184 እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አዲስ ዓመት በተሰጠው የተሰፋ ቃል ላይ ይቆማል። ለዚህ ዓመት ተሰፋ የሰጠውን ለመፈጸም፡ በዚህ ዓመት፡ በእሱ ላይ ይቆማል። ምንም ቢሆን፡ እነርሱ እንዳደረጉት፡ እኔም ወደፊት በፍቃዱ ላይ መሆን እፈልጋለሁ።

185 ልክ እንደ አብርሃም፡ መንታ መንገዱ ላይ ሲደርስ፡ እንዴት እንደሚያደርገው አላወቀም ነበር። እግዚአብሔር፡ "ወንድ ልጅ ልሰጥህ ነው" አለው። ለእርሱ ሃያ-አምስት ዓመታት ጠበቀ። በመጨረሻም ልጁ መጣ፡ ከዚያም እግዚአብሔር፡ "አሁን፡ በዚህ ልጅ፡ የብዙ አህዛብ አባት አደርግሃለሁ። እዚያ ላይ ውሰደውና ግደለው። ውሰደውና እረደው፡" ሃያ-አምሰት ዓመታት የጠበቀውን ያንኑ ነገር አጥፋው አለው። "ውሰደውና ግደለው።"

186 አብርሃም ፈጽሞ አልተጨነቀም። ፈጽሞ አላሰቸገረውም። እንጨቱን ሰብስቦ በትንሿ አህያ ላይ ጫነ፡ ልጁንም ወሰደ። ሊሰዋው፡ ወደ ተራራው ጫፍ አወጣው፡ ምክንያቱም አብርሃም ከሙታን መካከል እንደ አንዱ አድርጎ እንደተቀበለው ያውቅ ነበርና፥ የሳራ ማህፀን የሞተ ነበር፡ እርሱም መካን ነበር፡

ስለዚህ ምንም መንገድ አልነበረም። ልጁም... እርሱ መቶ ዓመቱ ነበር፡ እርሷ ደግሞ ዘጠና ዓመቷ ነበረች፡ ስለዚህ የመጣው በተስፋ ቃል ነበር። የተስፋ ቃሉን የሰጠው ያው አምላክ፡ ከሃያ አምስት ዓመታት በኋላ፡ “የአህዛብ አባት አደርግሃለሁ፡” አለው፡ መቶ-ዓመት ሆኖትም፡ እርሱና ባለቤቱ ልጁን ተቀበሉ። እግዚአብሔር እንዲሰዋው ከነገረው፡ እግዚአብሔር ሊያስነሳው ይችል ነበር። አሜን።

187 ወንድሞቼ፡ እግዚአብሔር ይመስገን። ጥሩ ስሜት ይሰማኛል። መንፈስ ቅዱስ ይሰማኛል። እንዴት ያለ ጥሩ ስሜት ይሰማኛል! ይህን አንድ ነገር አውቃለሁ፡ ዳግመኛ ሊያስነሳው ይችላል። ለዚህ ዘመን በተሰጠው ባልተበረዘው በዚያ በብርሃን ቃል ላይ እንቆማለን! ይህ ትውልድ ሲመጣ፡ በዚህ ትውልድ ላይ እንደሚያበሩ ብርሃኖች እግዚአብሔር ያስነሳናል። አሜን።

188 ስለዚህም፡ “የደቡብ ንግሥት በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልዷ ጋር ተነስታ፡ ይህንን ትውልድ ትፈርድበታለች፥ ምክንያቱም የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ ከምድር ዳር መጥታለችና፡ እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ፡” ማለቱ ምንም አያስገርምም። በዚያ ሩቅ ስፍራ የነበረችው፡ ያችህ ምስኪን ንግሥት፡ አረማዊት ሆና ሳለ፡ ያንን ብርሃን አይታ፡ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ በረሃውን አቋርጣ ብዙ ማይሎችን፡ ሶስት ወር በግመል ጀርባ ላይ ተጉዛ መጣች፡ እነርሱ ግን ልክ እዚያው ቆመው፡ ሰሎሞን የእርሱ ምሳሌና፡ ጥላ ሆኖ ሳለ ይህን አለማስተዋላቸው እንዴት ያለ ነገር ነው።

189 ከዚያም ዌስሊ፡ ሉተር፡ ሌሎችም ሁሉ፡ እዚያ ወደኋላ ያሉት የሐይማኖት ተቋማት መጡና አዩ፡ አሁን እየሆነ ላለው ነገር ምሳሌና ጥላ ሆነው፡ እነርሱ ግን ልክ በእርሱ ውስጥ አለፉ። ኦህ! መልካም።

190 ምክንያቱም፡ አዲሱ ዓመት የሚወሰነው በእግዚአብሔር ስለሆነ፡ በቃሉ ውስጥ ለመቆም ቁርጥ ውሳኔ አድርጉ። አሁን ወደ ማጠቃለያው ሰንመጣ፡ ሌሎቹ የተመረጡት ዘር፡ ቃሉን ባዩ ጊዜ በዘመናቸው እንዳደረጉት፡ ቃሉ ተመላለሱ በሚለው ውስጥ ተመላለሱ። ምን አደረጉ? በሌሎች ዘመናት የተመረጡ ዘሮች ከነበሩ፡ በውስጡ ተመላለሱ፡ እርሱ የማይወድቅ ቃል ነውና። ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል እንደሆነ ስንቶቻችሁ ታምናላችሁ? ኦህ፡ ማይ!

191 በቀደም የአንድ የተወሰነ የሐይማኖት ተቋም ሰዎች፡ ፕሮግራም ሰማሁ፡ ሚስተር ኤች. ኤም. ኤስ. ሪቻርድስ “ለዓመቱ መጽሐፍ እንደፃፈ” ተናገረ። እንደዚህ ካለ ሰው ጋር አለመስማማት አልፈልግም። ቡሆንም፡ የሰባተኛ-ቀን አድቬንቲስት ስለሆነ፡ ከሰባተኛ-ቀን አድቬንቲስት ትምህርት ጋር አልሰማማም፡ ነገር ግን ሰውዬውን በእርግጥ እወደዋለሁ። ነገር ግን ከእርሱ ጋር አልሰማማም። ያ የኤች. ኤም. ኤስ. ሪቻርድስ የአዲሱ ዓመት መጽሐፍ ሊሆን ይችላል።

192 ዳሩ ግን ለአዲሱ ዓመት፡ የእኔ መጽሐፍና የእናንተ መጽሐፍ፡ የአሮጌው ዓመት መጽሐፍ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቃሉ ሊኖርበት ተሰፋ ለተሰጠው ነገር ህያው አድርጉት። አዎ፡ ወዳጄ። ለሚመጣው እያንዳንዱ ዓመት፡ ለነበረው እያንዳንዱ ዓመት፡ እርሱ የተናገረውን የዘላለም ቃል የሚኖር የዘላለም አምላክ ነው፡ እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነትና በውስጡ ያለው እያንዳንዱ የተሰፋ ቃል፡ ባለፉት ዓመታት ውስጥ እንደነበረው ሁሉ ጸንቷል።

193 እግዚአብሔር ዓለምን በውሃ ሊያጠፋ ተስፋ እንደሰጠ፡ በሙሴ… ማለትም በኖኅ በኩል አጸናው።

194 ነጻ አውጪ ሊልክና፡ እስራኤልን ከግብፅ ሊያወጣ ተስፋ ሰጠ፥ ለአራት መቶ ዓመታት በእንግድነት ኖረው ነበር። ልክ ያንኑ አደረገ።

195 ዳዊትንም እንደሚያስነሳ ማለ፡ እንዲሁም ዳዊት እንዴት ልጅ—ልጅ እንደሚሆን፥ ክርስቶስ ልጁ እንደሚሆን፡ በዳዊት በኩል ክርስቶስ እንደሚመጣ። ያንን እንደሚያደርግ እንደማለ፡ ያንኑ አደረገ።

196 ከኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት በፊት፡ መጥምቁ ዮሐንስን ሊልክ ተስፋ ሰጠ። ልክ ያንኑ አደረገ።

መሲሕን ሊልክ ተስፋ ሰጠ። ልክ ያንኑ አደረገ።

197 ዓለም ወደ ትልቅ የድርጅቶች ሰብሰብ ውስጥ እንደምትገባና መዋቅር፡ አውሬ ተብሎ የሚታወቅ፡ ኃይል እንደምትሰራና፡ እዚያ ላይ በሰባቱ ኮረብቶች ላይ እንደምትቀመጥ ተስፋ ሰጠ። ልክ ያንኑ አደረገ።

198 ቤተክርስቲያን እንዴት እስከ ሞት ድረስ፡ እንደምታሳድዳቸው! ልክ ያንኑ አደረጉ።

199 በተሐድሶው ውስጥ እንዴት እንደወጡ! ልክ ያንኑ አደረጉ። በእያንዳንዱ ዘመን ውስጥ እንዴት እንደሚሆን ተስፋ ሰጠ!

200 ለዚህ ዘመንም ተስፋ ሰጠ። እርሱም በመጀመሪያው እንዳደረገው ሁሉ፡ ያንን ቃል ህያው እያደረገው፡ ዛሬም፡ እዚህ አለ። በእርግጠኝነት።

201 እያንዳንዱ የተስፋ ቃል ሲፈጸም፡ "ሞት በድል ሲዋጥ፡" ኢየሱስ ይመጣል፥ የመጨረሻውም ጸንቷል፡ ከዚያም በምድር ላይ የዘላለም ሰላምና፡ የዘላለም ሻሎም ይመጣል። የዘላለም ሻሎም፡ ሰላም፡ በምድር ላይ ያርፋል።

202 ኢየሱስ፡ የሰላም አለቃ በመጣ ጊዜ፡ ለምን ሰላም አልነበረም? ምክንያቱም ቃሉ ሁሉ በዘመኑ አልተፈጸመም ነበርና። ዛሬ እየፈጸመው ነው። ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ሀሳብ የነበረው፡ የተስፋ ቃሉ ሁሉ…

203 **ቃል** ማለት "የተገለጠ ሀሳብ" ማለት ነው። እግዚአብሔር፡ በሀሳቡ፡ አሰበው፡ በነቢያቱም በኩል ገለጠው፡ አሁን ደግሞ ሊፈጸም ይገባዋል። እና፡ ሲሆን፡ እንዳንሳሳትና በሚፈጸምበት ጊዜ በጨለማ ውስጥ እንዳንዳብስ እነዚህን ነገሮች፡ አስቀድሞ ነግሮናል።

204 አሁን፡ ክርስቶስን ለሁለተኛ ጊዜ ሊልክ ተስፋ ሰጥቷል። መቼም ቢያደርገው፡ ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ ሲመጣ፡ የዘላለም ሻሎም ይሆናል።

205 ወዳጆች ሆይ፡ ሰናጠናቅቅ፡ አዳምጡ። አስታውሱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የጥበብ ሁሉ ምንጭ ነው። ከዶክተር ከፒ.ኤች.ዲ.፡ ከኤል.ኤል.ዲ. አይመጣም። የሚመጣው ከእግዚአብሔር ቃል ነው።

206 በመቶዎች የሚቆጠሩ የነገረ መለኮት ዶክተሮች፡ እዚያ ተቀምጠው ነበር፡ አንድ የአስራ-ሁለት-ዓመት ትንሽ ልጅ ግን አፈረሳቸው፡ ምክንያቱም እርሱ ቃል ነበርና። ያ ትንሽ ልጅ ምንም ዓይነት ትምህርት አልነበረውም፡ ሆኖም ግን ቃል ነበር። ምክንያቱም ለዚያ ዘመን የተነገረው ብርሃን እርሱ ስለነበረ፡ ያንን ቃል እየገለጠው ነበር። ቃሉ በእርሱ ውስጥ ነበር። ሊሆን ይገባው ነበር።

ቃል ስለነበረ፡ የተናገረው መፈጸሙ ምንም አያስደንቅም። ተረድታችኋልን? የተረዳችሁ ሁሉ፡ “አሜን፡” በሉ። [ጉባኤው፡ “አሜን” አለ።—እርታዒ።] እርሱ ቃል ነበር።

207 መጽሐፍ ቅዱስን አስታውሱ፡ በሰው የተፃፈን-የዓመቱ-መጽሐፍ-የሚባለውን አይደለም። “የሰው ሁሉ ቃል ውሸት፡ የእኔ ግን እውነት ይሁን።”

208 የኑፋቄ ቡድኖችና ሐይማኖቶችና፡ የ—የመሳሰሉት፡ ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ ሲገቡ ሁሉንም ነገር በጣም ያወሳስቡታል። እግዚአብሔር በእንዲህ ዓይነት ቡድን ውስጥ ፈጽሞ ሰርቶ አያውቅም። ዛሬ ኢየሱስ ቢመጣ፡ ከሜቶዲስቶች፡ ከባፕቲስቶች፡ ከአድቬንቲስቶች፡ ከይሖዋ ምስክሮች፡ ከክርስቲያን ሳይንስ፡ ከጴንጤቆስጤዎች፡ ከፕሬስባይቴሪያኖች ጋር ይወግናልን? አይ፡ ወዳጄ። በእርግጠኝነት አይወግንም።

209 የየግል ጉዳይ ነው፡ እናንተና እግዚአብሔር። የሁለት ሰዎች አይን በተመሳሳይ ሁኔታ የሚያይ የለም፥ የትኛውም ሁለት አውራ ጣቶች አንድ ዓይነት አይደሉም። እግዚአብሔር የሚሰራው ከግለሰብ ጋር ነው። ትክክል መሆን አለመሆኑንስ እንዴት ታውቃላችሁ? ከዚያ ወደ ኋላ ተመልከቱና ከቃሉ ጋር መሆኑን ተመልከቱ። ከቃሉ ጋር ከሆነ፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እየሰራ ነው ማለት ነው፥ ካልሆነ ግን፡ ሌላ ነገር ከእርሱ ጋር እየሰራ ነው ማለት ነው። አያችሁ? በትክክል።

210 አስታውሱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የጥበብ ሁሉ ምንጭ ነው፡ የወደፊቱንም ተስፋ ሁሉ በውስጡ ይዟል። ሻሎም፡ የእግዚአብሔር ሰላም!

211 በአንድ ወቅት እንደተነገረው ታሪክ ነው፥ አንድ ትንሽ ልጅ አባቱን ለማየት ዕድሜው ከመድረሱ በፊት አባቱን አጣ፥ ገና ህፃን ልጅ እያለ አባቱ ሞተ። ከጊዜ በኋላ አስር፡ ወይም አስራ ሁለት ዓመት ገደማ ሆነው። ጆን የሚባል፡ ሌላ ወንድም ነበረው። ወደ ወንድሙ ሄደና፡ “ኧ፡ ጆን” አለው፡ እርሱም በብዙ ዓመታት የሚበልጠው ነበር፡ “አባዬን፡ አባዬን ታስታውሰዋለህ፡” አለው?

እርሱም፡ “አዎ” አለው።

እርሱም፡ “ምን ዓይነት ሰው ነበር” አለው?

212 እርሱም፡ “መቼም፡ እርሱ ረዥም ሰው ነበር፡ በጣም ጥሩ ሰው ነበር። ለእናቴ ሁልጊዜ ጥሩ ነበር፡ ለ—ለእኔም ደግ ነበር፡ ለሁሉም ሰው ደግ ነበር” አለው።

እርሱም፡ “ታዲያ፡ ስለእርሱ የምታውቀው ያን ብቻ ነው፡ ጆን” አለው?

213 እርሱም፡ “እንግዲህ፡ ይኸውልህ” አለው። እንዲህ አለ፡ “ሄንሪ፡” እንዲህ አለ፡ “ሁሉም ሰው እ—እኔ እርሱን እንደምመስል ይናገራል” አለው። “ሁሉም ሰው እኔ እንደ እርሱ ዓይነት ባህሪ እንዳለኝ ይናገራል፡” አለው።

214 እርሱም፡ “ኦህ፡ ያ ግሩም ነው! ማወቅ የምፈልገው ያንን ነው” አለ። እንዲህ አለ፡ “አንተን ሳይህ፡ አባቴን እየዋለሁ” አለው።

215 ይኸውላችሁ። ዓ—ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን ስታይ፡ ለዛሬው የተፃፈው ይህ ቃል፡ በእናንተ ውስጥ ሲሆን ነው።

216 በዳዊት ውስጥ ኢየሱስን የት ነው የምታዩት? ቃሉ በእርሱ በኩል በተገለጠ ጊዜ ነው።

217 በኤልያስ ውስጥ ክርስቶስን፡ እግዚአብሔርን እንዴት ነው የምታዩት፡ በዚያ ሠረገላ ወደ ሰማይ ሲወጣ፡ ኢየሱስን በኤልያስ ውስጥ አያችሁት? ምክንያቱም፡ ቃሉ ተረጋግጦ ነበርና።

218 በሙሴ ውስጥስ እንዴት ታዩታላችሁ? ኢየሱስ በሙሴ ውስጥ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚያ ይላል። አያችሁ፡ በትክክል፡ በምድረ በዳ ከሙሴ ጋር የነበረው የሚነደው ቁጥቋጦ እርሱ ነበር።

219 ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን እንዴት ያውቁታል? እነርሱ፡ እሱ፡ እርሱን በእናንተ ውስጥ ሲያየው፡ ኢየሱስን በእናንተ ውስጥ ሲያዩት ነው። ምክንያቱም፡ "እኔ የማደርገውን ስራ እናንተም ታደርጋላችሁ። እኔ ወደ አባቴ እሄዳለሁና፡ ከዚህ የሚበልጥ ታደርጋላችሁ፡" ብሏልና። ልክ ነውን? ዓለም የሚያውቀው፡ እንደዚያ ነው።

220 የጴንጤቆስጤ የአንድነት አማኞች ከጴንጤቆስጤ ከሁለትነት አማኞች ስለሚበልጥ፡ ወይም ሁለትነት አማኞች ከሥስትነት አማኞች፡ ወይም ካላችሁ ከማንኛውም ነገር ስለሚበልጥ አይደለም፥ ሜቶዲስት ከባፕቲስት ስለሚበልጥ አይደለም፥ ወይም ሳውዘርን ባፕቲስቶች ለባፕቲስት ቤተክርስቲያናት ሁሉ፡ ለ—ለፕሮቴስታንቶች ሁሉ የዚህን ዓመት ሽልማት ስለወሰዱ አይደለም። እንደተረዳሁት፡ በቁጥር ደረጃ፡ በዚህ ዓመት ከሌሎቹ ሁሉ የበለጠ አባላት አሏቸው። ያ የተለዩ አያደርጋቸውም። እግዚአብሔር በቁጥር አያውቃችሁም። አረማውያን በማንኛውም ጊዜ፡ በቁጥር ይበልጧችኋል። ካቶሊኮች ሁላችሁንም ይበልጧችኋል። ሞሃመዳኒዝም እነዚያን ሁሉ ይበልጣቸዋል። አያችሁ?

221 እናንተ የምትታወቁት ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ሲኖር፡ በህይወቱና፡ የዚህ ዘመን የተሰፋ ቃል ራሱን ሲያንፀባርቅ ነው። አያችሁ?

222 አሁን በሙሴ ውስጥ የተንፀባረቀው ያው ቃል በኤልያስ ውስጥ ሊንፀባረቅ አይችልም ነበር፡ ምክንያቱም ያ ሌላ ዘመን ነበርና። በኖኅ ውስጥ የተንፀባረቀው ያው ቃል በሙሴ ውስጥ ሊሆን አይችልም ነበር፡ ምክንያቱም፡ አያችሁ፡ ልክ ተሰፋ እንደተሰጠው፡ ኖኅ መርከብ ሰራ፡ ሙሴ ህዝብን መራ። በአንዱ ውስጥ የተንፀባረቀው ያው ብርሃን፡ በሌላኛው ውስጥ አልነበረም፡ ነገር ግን አንዱ ስለሌላው ይናገር ነበር።

223 አዲስ ኪዳን ሁሉ ስለዚህ ዘመን ይናገራል። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለዚህ ዘመን ይናገራል። ታዲያ፡ ማነው፡ አንዳንድ ሰው ነውን? ለዚህ ዘመን በሰጠው የቃሉ የተሰፋ ቃል ላይ፡ ብርሃኑን በማንፀባረቅ እየተገለጠ ያለው፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

224 ሰዎች እንደ እርሱ ስትኖሩ ሲያዩ፡ ባህሪያችሁንና ከቃሉ ጋር ያላችሁን አካሄድ ልክ እንደ እርሱ ሆኖ ሲያዩ፡ ቃሉ ሲገለጥ፡ ከዚያም ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን ያዩታል። "**ይህ** የሐይማኖት መግለጫ ምን ያስተምራል፡ **ያኛው** የሐይማኖት መግለጫስ ምን ያስተምራል፡" እያሉ፡ ወደ ሌላ ቦታ መመልከት አያስፈልጋቸውም? እናንተን ሲያዩ እግዚአብሔር ምን እንደሆነ ያውቃሉ።

225 ሻሎም፡ የእግዚአብሔር ሰላም በእናንተ ላይ ብርሃን ይሁን! በዚህ ዘመን የእግዚአብሔር ቃል፡ ሙሉ በሙሉ፡ ሲጸና እናንተም ያንን አይታችሁ ስታምኑት፡ ለእናንተ ሻሎም!

226 አዲሱን ዓመት በዚህ ተገናኙት፡ ዳዊት እንዳለው አድርጋችሁ እርሱን አስቀምጡ፡ "ሁልጊዜ በፊቴ አድርጌዋለሁ። በቀኜ ስለሆነ፡ አልታወክም።" በዚህ ዓመት ሞትን ብትጋፈጡ፡ ምን ለውጥ ያመጣል? እግዚአብሔር ሊያስነሳችሁ ተስፋ ሰጥቷል። አደጋ ቢገድላችሁ፡ ምን ለውጥ ያመጣል? የዘላለም ህይወት አላችሁ፡ "በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ።" አሜን። የሆነ ነገር ቢፈጠርስ? ምንም ቢሆን፡ በክርስቶስ ካለው፡ ከእግዚአብሔር ፍቅር ምንም ሊለየን አይችልም። "ረሃብ፡ አደጋ፡ እርቃንነት፡ ምንም ቢሆን፡ በክርስቶስ ካለው፡ ከእግዚአብሔር ፍቅር ምንም ሊለየን አይችልም።" እርሱም ቃል ነው። ሻሎም!

227 ራሳችንን ዝቅ እናርግ። አሁን ሁሉም ሰው ለአንድ አፍታ ራሱን ዝቅ ያድርግ። የእግዚአብሔር ሰላም!

228 "ድቅድቅ... " [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] "በኖኅ ዘመን እንደነበረው፡ ይበሉ፡ ይጠጡ፡ ያገቡ፡ ይጋቡ እንደነበረው፡" የሪኖ፡ ኔቫዳ፡ መላው የዝሙት መንደር፡ "የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜም እንዲሁ ይሆናል።"

229 "በሰዶም እንደነበረው፡" አብርሃም ኤሎሂም ሁሉን ቻይ የሆነው ብሎ በጠራው፡ በሰው አምሳል እግዚአብሔር በተገለጠ ጊዜ፥ እዚያ ቆሞ፡ ስጋ በላ፡ ወተት ጠጣ፡ ዳቦም በላ፥ ከኋላው፡ ከእርሱ ጀርባ፡ በድንኳኑ ውስጥ ሳራ ምን እያሰበች እንደነበረ ሊነግራት ቻለ። እርሱም፡ "ያ በሰው ልጅ መምጣት ጊዜ ዳግም ይመለሳል" ብሏል። "ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ዓለም ከእንግዲህ አያየኝም፥ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፡ እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ በእናንተም ውስጥ እሆናለሁና።"

230 አይሁዶች ወደ ምድራቸው እየተመለሱ ነው። በዚህ ዘመን፡ እየሆነ ያለው ነገር፡ ምን እየሆነ እንዳለ በግማሽ እንኳ እንድነግራችሁ አይፈቅድልኝም፡ ነገር ግን እያየነው ነው። ምንድነው? ቃሉ ተገለጠ።

231 ዕብራውያን ቃሉ ከተስፋ ቃል ጋር ተገልጦ ባዩት ጊዜ፡ ምን አደረጉ ብላችሁ ታስባላችሁ? ምድሪቱን ለቅቀው ለመውጣት ተዘጋጁ።

232 ዛሬ ዝግጁ ካልሆናችሁ፡ ወዳጄ፡ ይህን አዲስ ዓመት በትክክል ጀምሩ፡ እጃችሁን በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ፡ የእግዚአብሔርን ቃል በልባችሁ ውስጥ አድርጋችሁ ጀምሩት፡ እንዲህ በማለት፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ከዚህ ሲምፎኒ ውስጥ የትኛውን ክፍል እንድጫወት እንደምትፈልግ አላውቅም፡ ነገር ግን መከራን የምቀበልበት፡ የሚያሾፉብኝ፡ የሚሳለቁብኝ መጋጠሚያ ሲመጣ፡ አሁንም የአንተ ሲምፎኒ በእኔ ምክንያት እንዳይበላሽ ቦታዬን እይዛለሁ። ምንም ቢሆን፡ ከቃልህ ጋር በትክክል እቆያለሁ። እዚያው እቆያለሁ። ሞት በሬን ሲያንኳኳ፡ ያ የሲምፎኒ ክፍል ነው። ከዚያም፡ ሞት በሬን እንዳንኳኳ ሁሉ፡ ከነዚህ ቀናት በአንዱ፡ ትንሳኤም፡ እንደሚያንኳኳ አውቃለሁ፡ ዳግመኛም ታስነሳኛለህ። ያ የአንተ የሲምፎኒ ክፍል ነው። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ አካል እንድሆን ፍቀድልኝ፡ ትፈቅድልኛለህ? "

233 ያንን ሰዕላት መሳል የሚፈልግ ሰንት ሰው አለ፡ እንዲህ፡ “ወንድም ብራንሐም፡ ይህን አዲስ ዓመት ሰጀምር፡ ይህን ሰብሰባ ሰጀምር፡ አሁን፡ የራሴን አቋም ለመያዝ፡ ለተሰጠው ቃል ታማኝ ሆኜ ለመቆየት፡ ፈጽሞ ላለመውደቅና፡ ልክ እርሱ ተሰፋ በሰጠው መንገድ፡ በየዋህነትና በትህትና ለመኖር፥ እግዚአብሔር ህይወቴን ወሰዶ ወደ ታላቁ ሲምፎኒው ውስጥ እንዲያሰገባው፡ እግዚአብሔር በመጨረሻዎቹ ቀናት የሚያሰነሳው ያው ቡድን እንዲያደርገው አሁን ለእግዚአብሔር ቃል እገባለሁ። እጄን እነሳለሁ፡ ወንድም ብራንሃም፡ ለአንተ ሳይሆን፡ ለእግዚአብሔር እነሳለሁ። በፀሎት አስታውሰኝ” የሚል ሰው አለን? እግዚአብሔር፡ በያላችሁበት ይባርካችሁ። ጌታ ይባርካችሁ። የእኔም፡ እጆች ወደ ላይ ተነሰተዋል።

234 ጌታ ሆይ፡ ውሰደኝ። ጌታ አምላክ ሆይ፡ ልክ እንደ ይሁዳ፡ አዕምሮዬን፡ ተጨማሪ ዶላር ላይ፡ በሆነ የዓለም ፋሽን ላይ፡ ወይም የሆነ ሰው ጀርባዬን እያሻሸኝ፡ “ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ ይህ፡” በሚልበት ነገር ላይ እንዳደርግ ፈጽሞ አትፍቀድልኝ… አይ፡ አይ። እግዚአብሔር ሆይ፡ ያ በእኔ ላይ እንዲሆን ፈጽሞ አትፍቀድ። የተናቁት ጥቂት የጌታ ሰዎች ባሉበት መንገድ እሄዳለሁ። ለሰው ወንድም እሆናለሁ፡ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ፡ ጌታ ሆይ፡ ሰዎችን በሙሉ ልቤ እወዳለሁ። ጌታ ሆይ፡ ዳሩ ግን ከዚህ ቃል እንድወጣ ፈጽሞ አትፍቀድልኝ። በመጨረሻው ቀን መነሳት እፈልጋለሁ። በዚህ ታላቅ ሲምፎኒ ውሰጥ የተካተቱት ብቻ ናቸው፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ከሰዓት በኋላ ለማሰረዳት እንደሞከርኩት፡ የ—የሙዚቃ ኖታው መጨረሻ ላይ ሲደርሰ፡ ታላቁ ትንሳኤ ሲሆንና፡ መላእክት ሁሉ እጆቻቸውን ሲያጨበጭቡና ቅዱሳን እየገሰገሱ ሲገቡ የሚወጡት እነርሱ ናቸው። የምንፀልየው፡ በምንጫወተው በዚህ ታላቅ ድራማ ውሰጥ ያንን ድርሻ ለተወጡት ነው፡ ጌታ ሆይ።

235 በድራማ ውሰጥ ጭንብሎችን እንደሚቀይሩ እናውቃለን፡ ከአንዱ ነገር ወደ ሌላኛው ይመጣሉ፡ አንተም ያደረግኸው ያንን ነው። ከመንፈሰ፡ ከእግዚአብሔር፡ ከታላቁ ይሖዋ መጥተህ፡ የሰውን ጭንብል አደረግህ፡ የ—የ—የአንተን መልክህን ቀየርህ፥ ተለወጥህ። ድንኳንህን ተከልህ። ከእግዚአብሔር ዘንድ ወረድህ፡ የሰውን ልጅ ለመቤዠት ትሞት ዘንድ፡ ሰው ሆንህ። ጭንብልህን ቀየርህ።

236 ከዚያም ዳግመኛ ቀይረኸዋል፡ እዚህ በጻፍከው ቃል መሠረት በሚያምኑና በተግባር በሚያውሉ ሰዎች ውሰጥ ራሰህን ሸፍነሃል። ይህን የሚያዩ ዓይኖች ብፁዓን ናቸው፡ ይህን የሚቀበሉ ልቦች ብፁዓን ናቸው፡ ይህን የሚሰሙ ጆሮዎች ብፁዓን ናቸው፡ ሲምፎኒው ሲያበቃ ትንሳኤ ይሆናልና። እግዚአብሔር ሆይ፡ ሁላችንም በዚያ እንድንገኝ አድርግ፡ ታደርጋለህ? ይህን ትንሽ መንጋ ባርክ።

237 አባት ሆይ፡ እንደዚህ ሰንናገር፡ ይህ ቴፕ በዓለም ሁሉ ላይ እንደሚሄድ እናውቃለን። ዛሬ እዚህ የተቀመጠ ግሩም፡ ትንሽ ቡድን አለ፡ እዚህ ፊኒክሰ ውሰጥ ያለ የሚታይ ጉባኤ። እግዚአብሔር ሆይ፡ አሰራ አምሰት ዓመታት የፈጀ ከባድ ሰብከትና ተግሳፅ ነበር፡ እናም፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ አንተ ምክንያቱን ታውቃለህ፡ ፍቅር! ፍቅር መ—መቅጣት ነው። ፍ—ፍቅር ተግሳፅ ነው። ፍቅር ሰነ ሰርዓት ማሰተማር ነው።

238 እግዚአብሔር ሆይ፡ በዚህ ሳምንት ራሴን ከዚህ ህዝብ ጋር ላድርግ፡

ጌታ ሆይ፡ በቃልህ፡ ስነ ስርዓት እንድታስተምረን እንለምንሃለን። ኃይልህ በሽተኞችንና የተጎዱትን ሲያስነሳ፡ የዕውሮች አይኖች ሲከፈቱ፡ ታላቁ መንፈስ ቅዱስ በክፍሉ ውስጥ ሲታይ እንድንመለከት ፍቀድልን። እያንዳንዱ አገልጋይና እያንዳንዷ ቤተክርስቲያን በእሳት የተያያዘች ትሁን። ጌታ ሆይ፡ እየመጣ ያለው ቢዝነስመን ጉባኤ፡ በዚህች ከተማ ውስጥ ያለው፡ የእያንዳንዱን ቢዝነስማን ልብ፡ ለእግዚአብሔር በእሳት ያያይዘው። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ። ስለእርሱ መጠየቅና እንደሚሆን ከማመን በቀር፡ ምን ማድረግ እንዳለብን አናውቅም። በጌታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ራሳችንን ለአንተ አሳልፈን እነስጣለን።

አሁንም በእግሮቻችን እንቁም።

239 የንግግር ችሎታዬ ደካማ ነው፡ ቃላቶቼን በተሳሳተ መንገድ እጠራለሁ፡ ይህንም ለማለት ስለተሰማኝ ይህንን መናገር እፈልጋለሁ። "የእግዚአብሔር ሲምፎኒ" ስል ምን ማለቴ እንደሆነ የተረዳችሁ ስንቶቻችሁ ናችሁ፡ እጃችሁን የምታነሱት? እጃችሁን አንሱ። አመሰግናለሁ። መልካም። ታምኑታላችሁን?

240 እንግዲያውስ፡ እርሱ ሲምፎኒ ነው፡ አያችሁ። ወደ መጋጠሚያ ሲመጣ ታገኙታላችሁ፡ ሁሉም ሰው ግራ ይጋባል። እኔ መጋጠሚያ ብዬ እጠራዋለሁ። እኔ ሙዚቃ አላውቅም፥ እዚህ ውስጥ ያለ ሙዚቀኛ፡ እንግዲህ፡ ያ—ያ ሰው ትክክል ያልሆነውን አባባሌን ይቅር ይለኛል። ዳሩ ግን፡ እየመቱ፡ ነው፡ ሊያደርጉት የሚገባ ነገር ሊኖር ይገባል። በጣም ወደ ታች፡ ወደ ታች ይወርዳል፡ ምን እንደሆነ ትገረማላችሁ፥ ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ወደ ምቱ ከዘለቃችሁ፡ ትረዱታላችሁ። እግዚአብሔርን ልትረዱት የምትችሉበት ብቸኛው መንገድ ያ ነው፡ ወደ ቃናው ውስጥ በመግባት ነው።

241 "እርሱ ምንድነው? እኔ እንዴት? ወንድም ብራንሃም፡ እኔ እውነተኛ ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ወይም ጴንጤቆስጤ ነኝ።" ያ ቃናው አይደለም።

242 ቃናው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ቃል ነው። ቃሉ እግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔር ቃና፡ ቃሉን መታዘዝ ነው። ከዚያም ቃሉን ስትታዘዙ፡ ቃናውን በቀጥታ ወደ እናንተ ይመታዋል፡ ከዚያም ቦታችሁን ትይዛላችሁ። ወደ ታች፡ ወደ ታች፡ ወደ ታች ሲወርድ፡ ወደ ላይ ሲወጣ፡ ምንም ቢሆን፡ እነዚያን መጋጠሚያዎች ታውቃላችሁ።

አንዳንድ ጊዜ፥ "ኦህ፡ የልብ ህመሞችና ፈተናዎች" ትላላችሁ!

243 እግዚአብሔር፡ "የእኔን ሲምፎኒ እየመታሁ ሳለ፡ እርሱን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ለበጎ ይሆናሉ" አላለምን? ከዚያም እንደተጎዳችሁና እንደተመታችሁ፡ መከራን እንደምትቀበሉ፡ እንደሚያሾፉባችሁ ታገኛላችሁ። አስታውሱ፡ ያ በዚያ መንገድ የሚሄደው ክፍል ነው። ያ እንደዚያ ካልሆነ፡ እንግዲያውስ ሲምፎኒው ከቅኝት ውጭ ነው ማለት ነው።

244 ታላቁ አቀናባሪ በውስጡ ምን እንዳለ በትክክል ያውቃል። እርሱ ያውቃል። እርሱ ከመጀመሪያው፡ አውቋችኋል። ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ ስማችሁን በበጉ የህይወት መፅሐፍ ውስጥ አስፍሮታል። ያንን ታምናላችሁን? እርሱ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ያውቃል። ምንም ያህል ዝቅ ቢልና፡ ምንም ያህል ጨለማ ቢመስልም፡ በዚያ መንገድ መሆን አለበት።

245 ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ ሙሉ በሙሉ ወደ ሞት ጥላዎች ውስጥ ከገባ፡ “ትንሳኤና ህይወት እኔ ነኝ፥ ዳግመኛ አስነሳዋለሁ።” ታላቁ ዳይሬክተር ወርዶ ያችን በትር ወደ ታች ሲያወርዳት፡ ያኔ፡ “ከእንግዲህ ወዲህ ዘመን አይኖርም።” ያ መልአክ፡ በራእይ 10ኛው ምዕራፍ ላይ ያለው፡ አንዱን እግሩን በምድር ላይ ሌላኛውንም በባህር ላይ ሲያደርግና፡ በራሱም ላይ ቀስተ ደመና ሲኖር፡ “ከእንግዲህ ወዲህ ዘመን አይኖርም፡” ብሎ ማለ። ያ ጊዜ ሲመጣ፡ ከሙታን መካከል ትነሳላችሁ። የተቀሩት እዚያ ተኝተው ሳሉ፡ እናንተ ትገባላችሁ።

246 በሲምፎኒው ውስጥ ቆዩ። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ቆዩ። ምንም ያህል ከባድ ቢሆን፡ እግዚአብሔር በሚመታበት ቦታ ሁሉ፡ ልክ ከእርሱ ጋር ቆዩ።

247 አንዳንድ ጊዜ እሰሩን ለመበጠስ፡ ነፃ ሊያወጣችሁ ችግርን ያመጣል። እርሱ ያንን ያደርጋል። እናንተም፡ “ደህና፡ ምን እንደማደርግ አላውቅም” ትላላችሁ። እርሱ ያደርጋል። ምን ለውጥ ያመጣል? ድ—ድርሻውን እየተጫወታችሁ ብቻ ነው። በእጁ ውስጥ የያዛችሁ እርሱ ነው። እርሱ ይመራችኋል።

248 አስታውሱ፡ ሁሉም የሚደረገው በምልክት ነው። እየኖርንበት ያለነውን ዘመን፡ በምልክቱ እናውቀዋለን፡ ስለዚህ ሲምፎኒው ዛሬ ምን እንደሚያደርግ እናውቃለን። የመለያየት ጊዜ ነው፡ ብርሃንን ከጨለማው እየለየ ነው።

249 እንዳትረሱት፡ በአንድነት እንበለው፡ ምክንያቱም ይህንን እንዲናገር ይሰማኛልና፥ “ብርሃኑን ከጨለማው እየለየ ነው።” ደግመን እንበለው፥ “ብርሃኑን ከጨለማው እየለየ ነው።”

250 ያ የእግዚአብሔር ሲምፎኒ ነው። በሰማያት እያሳየው ነው። በጥቁር ስሌዳዎች ላይ እያሳየው ነው። በራሱ እያሳየው ነው። በቃሉ ተሰፋ ሰጥቶበታል። ጸንቶ አይተነዋል። ስንዴውን ከገለባው እየለየው ነው። ብርሃኑን ከጨለማው እየለየው ነው።

251 በፍጹም ልባችሁ፡ ታምኑታላችሁን? እንግዲያውስ፡ ያንን ግሩም መዝሙራችንን እንዘምር።

252 ለፓስተሮቼ አንድ ቃል መናገር እፈልጋለሁ፡ ለአንድ ደቂቃ ያህል። ወንድሞች፡ ጌታ ይባርካችሁ። ጉባኤዎቻችሁን አስናብታችሁ ወደዚህ ስላመጣችኋቸው አመሰግናለሁ። እዚያ ውጭ ላላችሁት ፓስተሮች፡ በእርግጥ አመሰግናችኋለሁ። እኔ እዚህ ያለሁት…

253 ወንድሞቼ፡ ሜቶዲስቶች፡ ባፕቲስቶች፡ ፕሬስባይቴሪያን ሊኖሩ ይችላሉ፡ ይህን ልበላችሁ። ልክ ለእናንተ እንደተናገርኩት ለጴንጤቆስጤዎችም በተመሳሳይ ሁኔታ እናገራለሁ፡ ይሰማችኋል? በተመሳሳይ ሁኔታ፡ አያችሁ። እርሱ…

254 ከአንድ ሰው ጋር፡ በጥብቅ፡ ካልተሰማማሁ፡ ሆኖም እርሱን መውደዴን ከቀጠልኩ… ምክንያቱም፡ ከእርሱ ጋር የማልስማማው፡ ዝም ብዬ ላለመስማማት ብዬ ከሆነ፡ ግብዝ ነኝ፥ እዚህ ላይ ለመቆም አልበቃም። ነገር ግን ከእርሱ ጋር ያልተሰማማሁት በህብረት በፍቅርና በመረዳት ምክንያት ከሆነ፡ ምንም ቢያደርግ፡ አሁንም የተወደደ ወንድሜ ነው። ከእርሱ ጋር እቆማለሁ። አዎን፡ በእርግጠኝነት። ያ በትክክል እውነት ነው። ያ በልቤ

ውስጥ ከሌለ፡ እንግዲያውስ እግዚአብሔር ከዚህ መድረክ ያውጣኝ፡ እኔ እዚህ ለመሆን አልበቃም። በትክክል። ይህንን የምለው ከፍቅር የተነሳና፡ እየመጣ ያለ ያየሁት ነገር ስላለ ነው። እርሱም እስከ አሁን ድረስ፡ በእርሱ ላይ እንድሳሳት ፈጽሞ አልፈቀደልኝም፡ ምክንያቱም ሁልጊዜም የእርሱ ቃል ስለሆነ። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

255 አሁን ለአንድ አፍታ ራሳችንን እናጎነብስ፡ ያንን ሁልጊዜ የምንዘምረውን ግሩም፡ የድሮ መዝሙር እንዘምር፡ "እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ።" ፒያኖ ተጫዋቹ፡ ወይም ማንም ቢሆን፡ ወይም ሙዚቃው ያላቸው ሰዎች፡ በዚያ ላይ ትንሽ ኖታ የሚሰጡን፡ ይመስለኛል። አዎ፡ መልካም፡ ያለ ሙዚቃ መዘመር እንችል እንደሆነ እንይ። አሁን ሁሉም ሰው በአንድነት፡ ራሳችንን እንዳጎነበስን እንዘምር።

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
አስቀድሞ ወዶኛልና
መዳኔንም ገዝቶልኛል
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

256 አሁን ቴፕ መቅረጹን ያቆሙ ይመስለኛል። አያችሁ፡ ይህ ቴፕ ወደየ...

64-0119 ሻሎም
ራማዳ Inn
ፊኒክስ, አሪዞና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org